ቀን ---------------------------

ቅጽ 004

በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት

የ ----------------------------------------------- ከተማ አስተዳደር/ ዞን ጽ/ቤት

## 35. ለመኖሪያ ቤት ግንባታ ሕብረት ሥራ ማህበር አባልነት የተዘጋጀ የማመልከቻ ቅጽ

1. የሕብረት ሥራ ማህበሩ ስም ------------------------------------------------------------ኃላፊነቱ የተወሰነ የመኖሪያ ቤት ግንባታ ሕብረት ሥራ ማህበር

2. የአመልካች ሁኔታ

2.1 የአመልካች ስም ------------------------------- የአባት ስም -------------------------------

የአያት ስም ---------------------------------- ጾታ ---------- ዕድሜ -------------

ብሔረሰብ -----------------------------

2.2 የእናት ስም --------------- የእናት አባት ስም --------------- የእናት አያት ስም ----------
-

2.3 የጋብቻ ሁኔታ

ያገባ/ያገባች　　　　የፈታ/ የፈታች

ያላገባ/ያላገባች　　　　በሞት የተለየ/ የተለየች

2.4 ያገባ/ ያገባች ከሆነ/ች የሚስት/የባል ስም ከነአያት -----------------------------------------

2.5 የአመልካቹ መኖሪያ ሥፍራ

- ክልል ------------------ ከተማ -------------
- ዞን /ክፍለ ከተማ ----------------- ወረዳ -------------------

●ቀበሌ ------------------ የቤት ቁጥር ------------------------

●የቤት ስልክ ቁጥር ---------------- የሞባይል ቁጥር -----------------

●የመታወቂያ ቁጥር /ፓስፖርት/ ቀበሌ/መ/ቤት -------------------------

## 3. የሥራና የገቢ ሁኔታ

3.1 የሥራ ሁኔታ

●የመንግሥት ተቀጣሪ የመንግሥታዊ ያልሆነ/ የግል ድርጅት ተቀጣሪ

●የግል ሥራ

3.2 የሥራ ቦታ

●የመ/ቤት ስም ---------------------------- የሚገኝበት ክልል -------------

● ዞን -------------- ከተማ -------------- ወረዳ -------------------

●የመ/ቤቱ ስልክ ቁጥር ------------------ የፖ.ሣ.ቁ ---------------

3.3 የአመልካች ወራዊ ገቢ /ብር/ --------------------

## 4. የሚፈልጉት ቤት ዓይነትና የክፍሉ ብዛት

4.1 የጋራ ሕንፃ ከሆነ

●ባለ አንድ መኝታ

●ባለ ሁለት መኝታ

●ባለ ሦስት መኝታ

●ባለ አራት መኝታ

●ሌላ

4.2. ባለ አንድ ፎቅ የከተማ ቤት

4.3. ቪላ

4.4. ከአካባቢ ዕቃ የሚገነባ ቤት

**5. በሕብረት ሥራ ማህበር የሚደራጁበት ሁኔታ**

- በመኖሪያ አካባቢ
- በመሥሪያ ቤት
- ከሌሎች ተመሳሰይ ፍለጎት ካላቸው ጋር

**6. በመሥሪያ ቤት የተደራጁ ከሆነ የቤቱ ወጪ የሚሸፈንበት ሁኔታ**

- ሙሉ በሙሉ በድርጅቱ የሚሸፈን
- በከፊል በድርጅቱ የሚሸፈን
- ሌላ ካለ ------------------------------------------

**7. የሚኖርበት / የምትኖርበት ቤት ሁኔታ**

- የቀበሌ ቤት
- የኪራይ ቤቶች
- ከግለሰብ በመከራየት
- ከሌላ ሰው ጋር በተደራቢነት
- በጥገኝነት
- ሌላ ---------------------------

## 8. እኔ ስሜ ከላይ የተጠቀሰው አመልካች፤

8.1 ከዚህ በፊት በማንኛውም በመንግሥት በተዘረጋው የቤቶች ልማት ኘሮግራም ውስጥ ያልተመዘገብኩ መሆኔን፣

8.2 በምደራጅበት ከተማ ውስጥ በራሴም ስም ሆነ በሚስቴ ስም (በባሌ ስም) የተመዘገበ የመኖሪያ ቤት ወይም የመኖሪያ ቤት ግንባታ ቦታ የሌለኝና ከዚህ በፊት ያለኝንም በሽያጭ ወይም በስጦታ ለሦስተኛ ወገን ያላስተላለፍኩና ከዚህ በፊት በቤቶች ልማት ኘሮግራም ተጠቃሚ ያልሆንኩ መሆኔን፤

8.3 ለምዝገባ ብቁ የሚያደርገኝ ከቤቱ ግንባታ ዋጋ ውስጥ 30% በመደራጀት ጊዜ ፣ ቀሪውን 20% ደግሞ ማህበሩ መሬት ሲያገኝ በዝግ የባንክ ሂሳብ የማስገባ መሆኔን፤

8.4 በከተማው ውስጥ ለተከታታይ ሁለት ዓመታት እየኖርኩ (እየሠራሁ) መሆኔን፣

8.5 የመንግሥት ቋሚ ሠራተኛ መሆኔን፣

8.6 በምወስደው ቤት ውስጥ በጋራ ሕንፃ ሕግ መሠረት ለመኖር ፍቃደኛ መሆኔን፤

8.7 እኔም ሆንኩ ባለቤቴ እየኖርን ያለነው በመንግሥት ቤት ውስጥ ከሆነ ቤቱን ከተረከብኩ በ30 ቀናት ውስጥ ያለሁበትን ቤት ቤቱን ለሚያስተዳድረው አካል ለማስረከብ ፍቃደኛ መሆኔን ፣

8.8 በዚህ የማመልካቻ ቅጽ ላይ የሞላሁት ሐሰት ሆኖ ከተገኘና ቤቱ ከመሠራቱ በፊት ከሆነ ውሉ የሚፈርስ መሆኑንና ቤቱን ከተረከብኩ በኋላ ከሆነ በሕግ ለመጠየቅ የተስማማሁ መሆኔን፣

8.9 ለመደፊት የሚጠየቁ መረጃዎችን ለምሣሌ የጣት አሻራና ሌሎች መረጃዎችን ለመስጠት ፍቃደኛ መሆኔን፣ እንዲሁም

8.10 በተራ ቁጥር 1 ሥር በተጠቀሰው የመኖሪያ ቤት ሕብረት ሥራ ማህበር ስም ከማህበሩ አባላት ጋር በፍላጎቴ ለመደራጀትና የመኖሪያ ቤት ለመሥራት ተፈላጊ ቅድመ ሁኔታና መስፈርት በተቀመጠው አዋጅና መመሪያ መሠረት የሞለሁ በመሆኔ ማህበሩ በአባልነት

እንዲቀበለኝና ከዚህ በላይ የሞላሁት መረጃ ሐሰት ሆኖ ከተገኘ በሕግ ተጠያቂ መሆኔን በመስማማት ይህን ቅጽ የሞላሁ መሆኔን በፍርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

የማህበሩ አባል ሙሉ ስም ------------------------------------------

ፊርማ ---------------------------

ቀን -------------------------

**ቀን ------------------------**

**ቅጽ 005**

**በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት**

**የ ------------------------------------------------ ከተማ አስተዳደር/ ዞን ጽ/ቤት**

**36. ለመኖሪያ ቤት ግንባታ ሕብረት ሥራ ማህበር አባልነት የተዘጋጀ የዲያስፖራ የማመልከቻ ቅጽ**

1. የሕብረት ሥራ ማህበሩ ስም ---------------------------------------------------------------ኃላፊነቱ የተወሰነ የመኖሪያ ቤት ግንባታ ሕብረት ሥራ ማህበር

2. የአመልካች ሁኔታ

2.1 የአመልካች ስም ------------------------------- የአባት ስም -------------------------------

የአያት ስም ----------------------------------- ጾታ ---------- ዕድሜ --------------

ብሔረሰብ ------------------ ዜግነት ----------------- የፓስፖርት ቁጥር -----------------

2.2 የእናት ስም --------------- የእናት አባት ስም --------------- የእናት አያት ስም -----------

2.3 የመኖሪያ ሥፍራ

2.3.1 ሀገር --------------------------

2.3.2 ከተማ ------------------------

2.4 የጋብቻ ሁኔታ

ያገባ/ያገባች የፈታ/ የፈታች

ያላገባ/ያላገባች በሞት የተለየ/ የተለየች

2.5 ያገባ/ ያገባች ከሆነ/ች የሚስት/የባል ስም ከነአያት ----------------------------------------

**3. የሚፈልጉት ቤት ዓይነትና የክፍሉ ብዛት**

3.1 የጋራ ሕንፃ ከሆነ

- ባለ አንድ መኝታ
- ባለ ሁለት መኝታ
- ባለ ሦስት መኝታ
- ባለ አራት መኝታ
- ሌላ

3.2 ባለ አንድ ፎቅ የከተማ ቤት

3.3 ቪላ

4. **የተወካይ መረጃ**

4.1 የተወካይ ስም ከነአያት --------------------------------------------------------

4.2 የተወካይ መኖሪያ ሥፍራ

- ክልል ------------------ ከተማ -------------
- ዞን /ክፍለ ከተማ ----------------- ወረዳ -------------------
- ቀበሌ ------------------ የቤት ቁጥር ------------------------
- የቤት ስልክ ቁጥር ---------------- የሞባይል ቁጥር -----------------
- የመታወቂያ ቁጥር /ፓስፖርት/ ቀበሌ/መ/ቤት ------------------------

5. እኔ ስሜ ከላይ የተጠቀሰው አመልካች፤

5.1 ከዚህ በፊት በማንኛውም በመንግሥት በተዘረጋው የቤቶች ልማት ኘሮግራም ውስጥ ያልተመዘገብኩ መሆኔን፣

5.2 በምደራጅበት ከተማ ውስጥ በራሴም ስም ሆነ በሚስቴ ስም (በባሌ ስም) የተመዘገበ የመኖሪያ ቤት ወይም የመኖሪያ ቤት ግንባታ ቦታ የሌለኝና ከዚህ በፊት ያለኝንም በሽያጭ ወይም በስጦታ

ለሦስተኛ ወገን ያላስተላለፍኩና ከዚህ በፊት በቤቶች ልማት ኘሮግራም ተጠቃሚ ያልሆንኩ መሆኔን፤

5.3 ለምዝገባ ብቁ የሚያደርገኝ ከቤቱ ግንባታ ዋጋ ውስጥ 50% በመደራጀት ጊዜ ፣ ቀሪውን 50% ደግሞ ማህበሩ መሬት ሲያገኝ በዝግ የባንክ ሂሳብ የማስገባ መሆኔን፤

5.4 በምወስደው ቤት ውስጥ በጋራ ሕንፃ ሕግ መሠረት ለመኖር ፍቃደኛ መሆኔን፤

5.5 እኔም ሆንኩ ባለቤቴ እየኖርን ያለነው በመንግሥት ቤት ውስጥ ከሆነ ቤቱን ከተረከብኩ በ30 ቀናት ውስጥ ያለሁበትን ቤት ቤቱን ለሚያስተዳድረው አካል ለማስረከብ ፍቃደኛ መሆኔን ፣

5.6 በዚህ የማመልካቻ ቅጽ ላይ የሞላሁት ሐሰት ሆኖ ከተገኘና ቤቱ ከመሠራቱ በፊት ከሆነ ውሉ የሚፈርስ መሆኑንና ቤቱን ከተረከብኩ በኋላ ከሆነ በሕግ ለመጠየቅ የተስማማሁ መሆኔን፣

5.7 ለመደፊት የሚጠየቁ መረጃዎችን ለምሣሌ የጣት አሻራና ሌሎች መረጃዎችን ለመስጠት ፍቃደኛ መሆኔን፣ እንዲሁም

5.8 በተራ ቁጥር 1 ሥር በተጠቀሰው የመኖሪያ ቤት ሕብረት ሥራ ማህበር ስም ከማህበሩ አባላት ጋር በፍላጎቴ ለመደራጀትና የመኖሪያ ቤት ለመሥራት ተፈላጊ ቅድመ ሁኔታና መስፈርት በተቀመጠው አዋጅና መመሪያ መሠረት የሞለሁ በመሆኔ ማህበሩ በአባልነት እንዲቀበለኝና ከዚህ በላይ የሞላሁት መረጃ ሐሰት ሆኖ ከተገኘ በሕግ ተጠያቂ መሆኔን በመስማማት ይህን ቅጽ የሞላሁ መሆኔን በፍርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

የማህበሩ አባል ሙሉ ስም -----------------------------------------

ፊርማ --------------------------

ቀን -------------------------

# የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የመኖሪያ ቤት ግንባታ ሕብረት ሥራ ማህበር አደረጃጀት መመሪያ ቁጥር 11/2007

## የኦሮሚያ ኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ቢሮ

**ታህሳስ 2007**

**ፊንፊኔ**

# ማውጫ


**ርዕስ** **ገጽ**

መግቢያ ........................................................ 2

**ክፍል አንድ**

1. አጭር ርዕስ ........................................................ 3
2. ትርጓሜ........................................................ 3
3. የተፈጻሚነት ወሰን ........................................................ 6

**ክፍል ሁለት**

4. አላማ ........................................................ 6
5. የመመሪያው መርሆዎች /Principles/........................................................ 7

**ክፍል ሦስት**

6. የአባላት ምዝገባ አጠቃላይ መስፈርቶች ........................................................ 7

**ክፍል አራት**

7. የቤቶች ዓይነት ፣ የግንባታ ዋጋና የሕብረት ሥራ ማህበሩ አባላት ብዛት ................ 12

**ክፍል አምስት**

8. የአደረጃጀትና ምዝገባ ሂደት ........................................................ 14

**ክፍል ስድስት**

9. ተግባርና ሃላፊነት ........................................................ 17

**ክፍል ሰባት**

10. ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች ........................................................ 25
11. ልዩ ልዩ ቅጾች ........................................................ 29-34

# የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የመኖሪያ ቤት ግንባታ ሕብረት ሥራ ማህበር አደረጃጀት መመሪያ ቁጥር 11/2007

## መግቢያ

የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት መስተዳድር የቤቶች ልማት ፖሊሲና ስትራቴጂን በመተግበር በኦሮሚያ ክልል ከተሞች ውስጥ የሚታየውን የመኖሪያ ቤቶች ችግር በቀጣይነት ለመፍታት ጥረት ሲያደርግ ቆይቷል፡፡ ይሁን እንጂ የኦሮሚያ ኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ቢሮ በክልሉ ያለው የመኖሪያ ቤት ችግር ከመሠረቱ ያልተቀረፈ መሆኑን በመገንዘብ ከዚህ በፊት በተጀመረው የ20/80 ቤቶች ልማት ኘሮግራም ላይ በተጨማሪ በአማራጭ ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው በ10/90 ኘሮግራምና መካከለኛ ገቢ ላላቸው በ40/60 በአቅማቸው መጠን ከመኖሪያ ቤት ችግር እንዲላቀቁ ለማድረግ ያለውን ፍላጎት ለይቷል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ በመንግሥት ድጋፍ ሊገነቡ የሚገባቸውን የቁጠባ ቤቶች ኘሮግራም ለማስቀጠል የተለያዩ ዝግጅቶችን በማድረግ ላይ የሚገኝ ስለሆነ በመንግሥት ድጋፍ የሚገነቡ ቤቶች እንዳሉ ሆነው የቤቱን ግንባታ ወጪ በራሳቸው 100% ችለው መኖሪያ ቤት ሊገነቡ የሚፈልጉና በሕግ የተቀመጠውን መሥፈርት ሊያሟሉ የሚችሉ ዜጎች በመኖሪያ ቤት ግንባታ ሕብረት ሥራ ማህበር ተደራጅተው የመኖሪያ ቤት ችግራቸዉን ለመቅረፍ በዚህ የቤቶች ልማት ኘሮግራም ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ፣

ከዚህ በፊት ለመኖሪያ ቤት ግንባታ ተደራጅተው የነበሩና አዲስ ሊደራጁ የሚፈልጉ ማህበራት አባሎቻቸው ለመኖሪያ ቤት ግንባታ ለመመዝገብ እንዲችሉ ሁኔታዎችን ማመቻቸት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፡

ቤት ለመሥራት የሚፈልጉ በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሀገር ያሉ ዜጎች በመኖሪያ ቤት ግንባታ ሕብረት ሥራ ማህበር ተደራጅተው የሚመዘገቡበትና የሚደራጁበት አካሔድ ግልጽ፣ አሳታፊና ተደራሽነት ያለው እንዲሆን፤ እንዲሁም ለሕገወጥ አሠራር እንዳይጋለጥ በማድረግ ከኪራይ ሰብሳቢነት የፀዳ እንዲሆንና በተለያዩ አካላት ኃላፊነት የተረጋገጠ ሆኖ መንግሥት በሚፈልገው የአፈጻጸም አቅጣጫ እንዲፈጸም ማድረግ ወሳኝ ሆኖ በመገኘቱ፣

ለመኖሪያ ቤቶች ግንባታ በሕብረት ሥራ ማህበር ተደራጅተው መቅረብ የሚፈልጉ ዜጎች አስፈላጊውን መሥፈርት ቀድመው እንዲያውቁ በማድረግ በተቀላጠፈ አገልግሎት ተስተናግደው በአጭር ጊዜ ውስጥ አደረጃጀታቸውን እንዲያጠናቅቁ ለማድረግ፣

ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት ሁሉ የግልና የጋራ ሐላፊነታቸውንና የሥራ ድርሻቸውን አውቀው ይህ የቤቶች ልማት ኘሮግራም ተሳክቶ ውጤታማ እንዲሆን የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የአስፈጻሚ አካላት አዋጅ ቁጥር 170/2004 አንቀጽ 4/17 ለኦሮሚያ ኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ቢሮ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

### ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

***ይህ መመሪያ "የኦሮሚያ የመኖሪያ ቤቶች ግንባታ የሕብረት ሥራ ማህበር አደረጃጀት መመሪያ ቁጥር 11 /2007" ተብሎ ይጠራል፡፡***

2. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፣

1) "***መንግሥት***" ማለት የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ነው፡፡

2) "**ቢሮ** "ማለት የኦሮሚያ ኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ቢሮ ነው፡፡

3) "**ጽ/ቤት**" ማለት የዞን ኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ጽ/ቤት ነው፡፡

4) **"የከተማ አስተዳደር"** ማለት በየትኛውም ደረጃ ላይ ያለ ከተማ ሆኖ የከተማነት ሕጋዊ ሰውነት ያለው በሙሉ ማለት ነው፡፡

5) **"የመሬት ኤጀንሲ**" ማለት የኦሮሚያ ከተማ መሬት ልማትና ማኔጅመንት ኤጀንሲማለት ነው፡፡

6) **"የቤት ኤጀንሲ"** ማለት የኤሮሚያ ቤቶች ግንባታና ልማት ኤጀንሲ ማለት ነው፡፡

7) **"የሕንፃ ሹም"** ማለት በአዋጅ ቁጥር 174/2004 የሕንፃ አዋጅ እንዲያስፈጽም ሥልጣን የተሰጠው ሰው ማለት ነው፡፡

8) "**ዩኒየን**" ማለት ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ተመሳሳይ  አላማ ያላቸው መሠረታዊ የመኖሪያ ቤት ግንባታ ሕብረት ሥራ  ማህበራት በአንድ ላይ ተደራጅተው ያቋቋሙት  ሁለተኛ ደረጃ የሕብረት ሥራ ማህበር ማለት ነው

9) **"አዋጅ"**  ማለት የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት መስተዳድር አስፈጻሚ አካላት አዋጅ ቁጥር 170/2004 ና የፌዴራል ሕብረት ሥራ ማህበር አዋጅ ቁጥር 147/1991 ነው፡፡

10) "**ደንብ**"  ማለት የፌዴራል ሕብረት ሥራ ማህበር ቁጥር 106/ 2004 ማለት ነው፡፡

11) **"የሊዝ መነሻ ዋጋ"** ማለት ዋና ዋና መሠረተ ልማቶችን ለመዘርጋት የሚያስፈልግ ወጪ ፣ በመሬቱ ላይ የፈሰሰ ንብረት ለማንሳት ወይም ከመሬቱ ላይ ለሚነሱ ሰዎች የሚከፈል ካሣና ሌሎች ወጪዎችን ከግምት ውስጥ ያስገባ የሊዝ መነሻ ዋጋ ማለት ነው፡፡

12) **"አደራጅ አካል"** ማለት በአዋጅ  ቁጥር 170 /2004 አንቀጽ 4/17/ ለኦሮሚያ ኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ቢሮ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የመኖሪያ ቤት ግንባታ ሕብረት ሥራ ማህበር እንዲያቋቁም ሥልጣን  የተሰጠው የኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ቢሮ ፣  የከተማ አስተዳደር፤ የዞን እንዱስትሪና ከተማ ልማት ጽ/ቤት ማለት ነው፡፡

13) "**ማህበር**" ማለት በአዋጅ ቁጥር 170/2004 አንቀጽ 3/2 መሠረት ለመኖሪያ ቤት ግንባታ የተቋቋመና የተመዘገበ የሕብረት ሥራ ማህበር ማለት ነው፡፡

14) "**ነባር** ማህበር" ማለት ይህ መመሪያ ከመውጣቱ  በፊት ለመኖሪያ ቤት ግንባታ ተቋቁሞና ተመዝግቦ ሕጋዊ ሰውነት ያገኘ የሕብረት ሥራ ማህበር ማለት ነው፡፡

15) **"አዲስ ማህበር"** ማለት ይህ መመሪያ  ወጥቶ ሥራ ላይ  ከዋለ በኋላ  ለመኖሪያ  ቤት ግንባታ ተቋቁሞና ተመዝግቦ ሕጋዊ ሰውነት ያገኘ የሕብረት ሥራ ማህበር ማለት ለው፡፡

16) **"መሥሪያ ቤት"** ማለት በዚህ መመሪያ መሠረት ለሠራተኞቹ ሙሉ የቤት ግንባታ ወጪ የከፈለና የመኖሪያ ቤት ለመስራት ፍቃደኛ  የሆነ መሥሪያ ቤት ማለት ነው፡፡

17) "**ዲያስፖራ**" ማለት የኢትዮጵያ ዜጋና በትውልድ ኢትዮጵያ ሆነው ውጭ ሀገር የሚኖሩ ማለት ነው፡፡

18) **"ተመላሽ ዲያስፖራ"** ማለት የኢትዮጵያ ዜጋ ሆነው ውጭ ሀገር ቆይተው በተለያየ ምክንያት ከውጭ ሀገር ተመልሰው ከሁለት ዓመት በላይ ሀገር ውስጥ የኖሩና በተለያዩ ሥራዎች ላይ የተሠማሩ ማለት ነው፡፡

19) "**ሚስዮን**" ማለት የፌዴራል መንግሥት ውጭ ሀገር ያቋቋመው ወይም የሚቋቁመው የኤምባሲ ወይም ቆንስላ ጽ/ቤት ማለት ነው፡፡

20) "**ዲፕሎማት**" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት ከውጭ ጉዳይ ሚ/ር ወይም ከሌላ መንግሥታዊ መ/ቤት በውጭ ግንኙነት ሥራ ላይ ተመድቦ የሚሠራ ሠራተኛ ማለት ነው፡፡

21) **"የውክልና ማስረጃ"** ማለት ሕጋዊ ሥልጠን በተሰጠው አካል በውልና ማስረጃ ጽ/ቤት ወይም በሚስዮን ዘንድ በአካል ቀርቦውክልና ተሰጥቶት በውጭ ጉዳይ ሚ/ርና በውልና ማስረጃ ጽ/ቤት የፀደቀ ማስረጃ ማለት ነው፡፡

22) "**ቤት**" ማለት በሕጋዊ ሁኔታ ተሠርቶ ለመኖሪያ ቤትነት የሚውል ቤት ማለት ነው፡፡

23) **"የከተማ ቤት"** ማለት የባለ አንድ ፎቅ (G+1 ፣ G+2 )ሆኖ አነስተኛ ግቢና ራሱን የቻለ መግቢያና መውጫ ያለውና ከጎረቤቱ ጋር ግድግዳው የተያየዘ ማለት ነው፡፡

24) "**አፓርታማ**" ማለት የባለ አራትና ከዚያ በላይ ፎቅ ሆኖ በተፈቀደው የመሬት መጠቀሚያ ፕላን መሠረት ባለቤትነቱ የግል የሆነ የጋራ ቤት ማለት ነው፡፡

25) "**ቪላ**" ማለት በብሎኬት ወይም በድንጋይና በስሚንቶ ተገንብቶ ራሱን የቻለ ግቢ ያለው ቤት ማለት ነው፡፡

26)"**ከአካበቢ የሚገኝ የቤት ግንባታ ዕቃ**" ማለት በከተማ የህዝብ ብዛቱ 10000 ና ከዚያ በታች ለሆነና በትላልቅ ከተሞች በልዩ ሁኔታ የከንቲባ ኮሚቴ ቤቱ የሚሠራበትን ደረጃና የማህበሩን ተጨባጭ አቅም ማዕከል አድርጎ በሚወስነው ለመኖሪያ ቤት ግንባታ የሚውል ዕቃ ማለት ነው፡፡

27) **"ዝግ ሂሳብ"** ማለት የመኖሪያ ቤት ግንባታ ሕብረት ሥራ ለቤት ግንባታ ወጪ በማህበሩ ስም በማይንቀሳቀስ ዝግ የባንክ ሂሳብ ውስጥ የሚያስቀምጥ ገንዘብ ማለት ነው ፡፡

28) **"ባንክ"** ማለት የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ማለት ነው፡፡

29)**“ራስ አገዝ የሕብረት ሥራ”** ማለት የሕዝብ ብዛታቸው ከ2000-10000 የሆነ ጥቃቂን ከተሞች ሆነው በመኖሪያ ቤቶች ግንባታ ሕብረት ሥራ ማህበር ተደራጅተው የጉልበታቸው ሂሳብ ለቤት ግንባታ በሚወጣው ወጪ ውስጥ የሚታሰብላቸው ማለት ነው፡፡

30)**“የከተማ ደረጃ”** ማለት በአዋጅ ቁጥር 165/1995 አንቀጽ 6 መሠረት ከ1-4 የተሰጠ የኦሮሚያ ከተሞች ደረጃ ማለት ነው፡፡

31) **“የቤት ልማት ፕሮግራም”** ማለት መንግሥት የመኖሪያ ቤት ችግር ለመቅረፍ ያወጣቸው 10/90፣20/80፣ 40/60 ፕሮግራምና የመኖሪያ ቤት ግንባታ ሕብረት ሥራ ማህበር ማለት ነው፡፡

32) “**ፕላን**” ማለት የአንድን ሕንፃ መጠን አይነትና ስፋት ፣ እንዲሁም የሕንፃውን የግንበታ ስልት ዲዛይንና ዕቃ የሚያሳይ መረጃ ወይም ሞዴል ሲሆን አርኪቴክቸር፣ ስትራክቸር ፣ ሳኒተሪ፣ ኤሌክትሪክ፣ ሜካኒካል ሆኖ የእሳት አደጋ መከላከያና ሌሎች የዲዛይን ሥራዎችን ይጨምራል፡፡

33)“**ሰው”** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕጋዊ መንገድ ሕጋዊ ሰዉነት የተሰጠው ድርጅት ማለት ነው፡፡

### 3. የጾታ አገላለጽ

በዚህ መመሪያ ውስጥ በተባዕት ጾታ የተገለጸው እንስታይ ጾታንም ያካትታል፡

### 4. የአፈጻጸም ወሰን

ይህ መመሪያ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት መስተዳድር ከተሞች በሀገር ውስጥም እና በውጭ ሀገር የሚኖሩ ዜጎች በመኖሪያ  ቤት ግንባታ የሕብረት ሥራ ማህበር ተደራጅተዉ ሕጋዊ ሰውነት ባገኙት ሁሉ ላይ ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡

## ክፍል ሁለት

## የመመሪያው ዓላማና መርሆዎች /Principles/

### 5. ዓላማ

1. በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት መስተዳድር ውስጥ በሕብረት ሥራ ማህበር ተዳራጅተው የመኖሪያ ቤት ለመሥራት የሚፈልጉ ሰዎች ማሟላት ያለባቸውን ቅድመ ሁኔታዎችና ያለውን ኃላፊነትና ግዴታ እንዲያውቁ በማድረግ ግልጸኝነትና ፍትሓዊነት ያለው የአዳረጀጀትና የምዝገባ ሥርዓት ለመዘርጋት፣

2. በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት መስተዳድር ፍቃደኝነትና ፍላጎት ያላቸው ዜጎች በቤት ግንባታ የሕብረት ሥራ ማህበር ተዳራጅተው ገንዘባቸው፣ ዕውቀታቸውን ፣ ጉልበትና ጊዜያቸውን በማቀናጀት ያለባቸውን የመኖሪያ ቤት ችግር ቅንጅት ባለው ጥረት መፍታት እንዲችሉ አማራጭ ዕድል እንዲያገኙ ለማድረግ፣

3. ከዚህ በፊት በመኖሪያ ቤት ግንባታ ሕብረት ሥራ ማህበር ተደራጅተው በተለያዩ ምክንያቶች እስካሁን የመኖሪያ ቤት ' መሥሪያ ቦታ ያላገኙትና ገንዘባቸውን በባንክ አስገብተው በመጠባበቅ ላይ ያሉ የማህበራቸውን ውሰጣዊና ውጫዊ ችግሮች በመፍታት በዚህ የቤቶች ልማት ኘሮግራም መጠቀም እንዲችሉ ግልጸኝነትና ተጠያቂነት ያለው አሠራር ለመዘርጋት፣

4. በመኖሪያ ቤቶች ግንባታ ሕብረት ሥራ ማህበር አዲስ መደራጀት የሚፈልጉ በዚህ የቤቶች ልማት ኘሮግራም መጠቀም እንዲችሉ ግልጸኝነትና ተጠያቂነት ያለው አሠራር ለመዘርጋት፣

5. መንግሥት ባስቀመጠዉ ፓሊሲ አቅጣጫ ወጪ ቆጣቢ የጋራ መኖሪያ ቤቶች ለመገንባት በሕብረት ሥራ ማህበር የሚደራጁ ነዋሪዎች የተቀናጀ ድጋፍና ዕርዳታ እንዲያገኙ ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር፣

6. በዚህ የቤቶች ልማት ኘሮግራም ውስጥ ባለድርሻ የሆኑ አካላት የአዳረጃጀት፣ የተግባርና የሃላፊነታቸውን አቅጣጫ ለማሳየትና የተቀናጀ ድጋፍ ለማድረግ፣

7. ሥልጣኑ ለኦሮሚያ ኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ቢሮ ቢሰጥም የመኖሪያ ቤቶች ግንባታ ሕብረት ሥራ ማህበር ጉዳይ የሚያስፈጽም መዋቅር ስላልተደራጀ አንድ ደራጅ ለማድረግ፤

**6. የመመሪያው መርሆዎች /Principles/**

በፌዴራል ሕብረት ሥራ ማህበር አዋጅ ቁጥር 147/1991 የቤቶች ግንባታ ሕብረት ሥራ ማህበር አደረጃጀት ውስጥ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት መስተዳድር ውሰጥ ፣

1. የመኖሪያ ቤት ግንባታ ሕብረት ሥራ ማህበርን አስፈላጊ መሥፈርት ሁሉ ለሚያሟሉ አባላት ያለአንዳች ልዩነት እኩል ተጠቃሚ የሚያደርጋቸውን አሠራር መከተል፣

2. የመኖሪያ ቤት ችግርን በራስ ገንዘብ፣ ዕውቀትና ጉልበት ለመፍታት የሚደረገውን ርብርብ ለመደገፍ የሚያበረታታ እቅጣጫ ለመከተል፣

3. በመኖሪያ ቤቶች ሕብረት ሥራ ማህበር የሚደራጁ አባላት የማህበሩን ውሳኔዎች የማክበር ግዴታ እንዳላቸውና የመሳተፍ መብታቸው እንዲከበር በማድረግ ዲሞክራሲያዊ አመለካከት እንዲጎናፀፉ ለማድረግ፣

4. ከኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከትና ድርጊት የፀዱ እንዲሆኑ ለማድረግ፣

5. ይህ የመኖሪያ ቤቶች ግንባታ የሕብረት ሥራ ማህበር አደረጃጀት የባለድርሻ አካላት የቤቶች ልማት ፕሮግራም ተሳትፎን የሚያረጋግጥ አንዲሆን ለማድረግ፡፡

## ክፍል ሦስት

## የመኖሪያ ቤት ሕብረት ሥራ ማህበር አባል ሆኖ በመደራጀት ለመመዝገብ የሚያስፈልጉ መስፈርቶች

### 7. አጠቃላይ መስፈርቶች

በፌዴራል ሕብረት ሥራ ማህበር አዋጅ 147/1991 አንቀጽ 13 ለሕብረት ሥራ ማህበር የተደነገገው መስፈርት እንደተጠበቀ ሆኖ ለዚህ የቤቶች ልማት ፕሮግራም ሲባል፣

ሀ. ዕድሜው 18 ዓመትና ከዚያ በላይ ሆኖ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት መስተዳድር ውስጥ ነዋሪ የሆነና ባሁኑ ጊዜ ዲያስፖራ ሆኖ ውጭ ሀገር የሚኖር፣

ለ. በከተማው ውስጥ በተከታታይ ለ2 ዓመትና ከዚያ በላይ የኖረና በመኖር ላይ ያለ፣

ሐ. የመንግሥት ሠራተኛ ከሆነ በመንግሥት መሥሪያ ቤት ሠራተኛ ሆኖ እየሠራ ያለ፣

መ. መኖሪያ ቤቱ በቋሚነት በከተማው ውስጥ ሆኖ ለተከታታይ 2 ዓመት በከተማው ውስጥ ባይኖር እንኳ፣

1. በሥራ ምክንያት ሌላ ቦታ እየሠራ ስለመሆኑ ማስረጃ የሚያቀርብ፣
2. ለትምህርት፣ ለህክምናና በመንግሥት የሥራ ግዳጅ ሌላ ሀገር ለመኖሩ ከሚመለከተው አካል ላይ ማስረጃ ማቅረብ የሚችል፣
3. ወደ ውጭ ሀገር ተሰድዶ ወደ ሀገር የተመለሰ፣
4. የዲፕሎማትነት ማስረጃ የሚያቀርብ፣

ሠ. ሙሉ የግንባታ ክፍያ መክፈል የሚችልና የሕብረት ሥራ ማህበር የአባልነት ምዝገባ ክፍያ መክፈል የሚችል፣

ረ. የሀገር ውስጥ ነዋሪ ከሆነ የቤቱን ግንባታ ወጪ ግምት 20% ሲደራጅና 30% መሬቱ በእጁ ሲገባ በባንክ የማይንቀሳቀስ ሂሳብ / block account/ ማስገባት የሚችል፣

ሰ. ግንባታውን ለማጠናቀቅ ቀሪውን ክፍያ 50% በሂደት በመቆጠብ ግንባታው እስኪጠናቀቅ ድረስ ገቢ ማድረግ የሚችል፣

ሸ. ዲያስፖራ ከሆነ የቤቱን ግንባታ ወጪ 50% ሲደራጅና ቀሪዉን 50% መሬቱ በእጁ ሲገባ በባንክ የማይንቀሳቀስ ሂሳብ ማስገባት የሚችል፣

ቀ. የማህበሩን መተዳደሪያ ደንብ፣ ዓላማዎችና እሴቶች ለማክበርና ለማስከበር ፍቃደኛ የሆነ፣

በ. ከዚህ በፊት በራሱም ስም ሆነ በባለቤቱ /ቷ/ ስም ከከተማው ውስጥ የመኖሪያ ቤት ወይም የመኖሪያ ቤት ቦታ የሌለው ወይም ኖሮት ለሦስተኛ ወገን ያላስተላለፈ፣

ተ. ከከተማዉ ዉስጥ በቤቶች ልማት ኘሮግራም ዕድል ያላገኘና ወደ ፊት ለማግኘት ያልተመዘገበ ወይም የተመዘገበ ከሆነ ለመሰረዙ ማስረጃ ማቅረብ የሚችል ወይም ቃል ገብቶ የፈረመ፣

ቸ. የሕብረት ሥራ ማህበር አባል ሆኖ በመኖሪያ ቤት ሕብረት ሥራ ማህበር ሲመዘገብ በአቅሙ በአካባቢው የግንባታ ዕቃ የሚገነባቤት፣ ቪላ፣ የከተማ ቤት፣ አፓርታማ ከሆነ የባለአንድ ፣ ባለሁለት ፣ ባለሦስትና ባለአራት መኘታ ቤት ለመደራጀት ፍቃደኛ የሆነ፣

ኀ. በመኻል ከተማ በመልሶ ማልማት ኘሮግራም በተያዘ ቦታ ላይ የመኖሪያ ቤት ማህበር ሆኖ የሚደራጅ ማህበር ወይም ዩኒየን ከሆነ የከተማ መሬት ልማትና ማኔጅመንት በሚያወጣው ግምት መሠረት ቤታቸው ለሚፈርስባቸው ሰዎች ካሣ ለመክፈል ቃል የሚገባ፣

ነ. ቤታቸው ለሚፈርስባቸው ባለንብረቶች የሚከፈለው የካሣ ግምት መንግሥት ለልማት ለሚነሱ ሰዎች እየከፈለ ባለው ግምት የሚሰላ ይሆናል፡፡

ኘ. እንደ አስፈላጊነቱ የጣት አሻራ ለመስጠት ፈቃደኛ የሆነ፡፡

አ. የተደራጀው የሕብረት ሥራ ማህበር የሚጠራበትን ስም ወይም ስያሜ ይኖረዋል፡፡

## 8. የሕብረት ሥራ ማህበር አባል ሆኖ ለመመዝገብ የሚያስፈልጉ ተጨማሪ መስፈርቶች

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7 ሥር የተዘረዘሩት መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆነው ማንኛውም የመኖሪያ ቤት ሕብረት ሥራ ማህበር ተመዝጋቢ፣

1) በነባሩ የመኖሪያ ቤት ግንባታ ሕብረት ሥራ ማህበር ኘሮግራም ተጠቃሚ ለመሆን፤

ሀ. ከዚህ በፊት ካደራጀው አካል ላይ የመኖሪያ ቤት ሕብረት ሥራ ማህበር ሆኖ መደራጀቱን በአካል ወይም በተወካዩ በኩል በመቅረብ የመኖሪያ ቤት ሕብረት ሥራ ማህበር አባል መሆኑን በማረጋገጥ በድጋሚ መደራጀትና መመዝገብ አለበት፡፡

ለ. ገንዘባቸው በማህበሩ ስም በባንክ ተይዞ የሚገኝ የተደራጁ ነባር ማህበራት ከእያንዳንዱ አባል በሚፈለገው እና በአሁኑ ወቅት ባለው የግንባታ ወጪ ግምት በተጨማሪ ወይም ልዩነቱን በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ዝግ ሂሳብ ገቢ ካደረገ፤

ሐ. የነባር ማህበሩ አባላት የውጭ ሀገር ነዋሪዎች /ዲያስፖራ/ ከሆኑ በአካል በመቅረብ ወይም በውጭ ጉዳይ ሚ/ር በኩል በሚወክለው ሰው አማካይነት የሕብረት ሥራ ማህበሩን በሚያደራጀው አካል በመቅረብ ከተመዘገበ፤

መ. በአንቀጽ 8 /1/ /ሐ/ መሠረት አንድ የተመዘገበ አካል የቤቱን የግንባታ ወጪ በኢትዮጵያ ኤምባሲ በኩል ወይም ከውጭ ጉዳይ ሚ/ር ጋር በመወያየት የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በሚያመቻቸው የቁጠባ ሥርዓት በዚያን ጊዜ ባለው የውጭ ምንዛሪ ግምት ጋር በተመጣጠነ አኳኋን በባንክ ዝግ ሂሳብ ገቢ ካደረገ፤

ሠ. የሀገር ውስጥም ሆነ የውጭ ሀገር የሕብረት ሥራ ማህበር አባል ከላይ የተጻፉትን መስፈርቶች በማረጋገጥ ከዚህ መመሪያ ጋር የተዘጋጀ ቅጽ ቁጥር 004 ና 005 ተሞልቶ ከቀረበ፤

ረ. በአካባቢዉ ባለዉ ከተማ ለመኖሪያ ቤት ግንባታ ማህበር በማህበር ለመደራጀት ፍላጎት ያለዉ አርሶ አደርና አርብቶ አደር ለቤት ግንባታ የሚያስፈልገዉን የገንዘብ አቅም ያለዉ መሆኑን የሚያረጋግጥ የድጋፍ ደብዳቤ ከወረዳ፣ ከዞንና ከግብርና ጽ/ቤት ካቀረበ፡፡

2) በአዲሱ የመኖሪያ ቤት ግንባታ ሕብረት ሥራ ማህበር አባላት የሚደራጁበት ሁኔታ

ሀ. አዲስ የመኖሪያ ቤት ግንባታ ሕብረት ሥራ ማህበር አባል ሆኖ ለመደራጀት የሚፈልግ በፍላጎትና በገንዘብ አቅም የሚመሳሰል ሆኖ ሲገኝ ከዚህ መመሪያ ጋር በተዘጋጁ ቅጾች ላይ ሞልቶ በማቅረብ ፍቃደኛና አብሮ ለመስራት የተስማማ መሆኑን በሚያደራጀው አካል ዘንድ ቀርቦ በማፅደቅ በማህበር ሊደራጅ ይችላል፡፡

ለ. የተለያዩ መሥሪያ ቤቶች ሠራተኞች ለመኖሪያ ቤት ግንባታ ሕብረት ሥራ ማህበር በመደራጀት ተጠቃሚ ለመሆን፣

1. የመሥሪያ ቤቱ ሠራተኞች ተመሳሳይ ፍላጎትና የገንዘብ አቅም ያላቸው መሆናቸውን በማረጋገጥ ከዚህ መመሪያ ጋር በተዘጋጁ ቅጾች ላይ በመሙላት የሕብረት ሥራ ማህበርን በሚያደራጀው አካል ዘንድ ቀርበው መመዝገብ አለባቸው፡፡

2. ለሠራተኞቻቸው ቤት መሥራት የሚፈልጉ መሥሪያ ቤቶች በቅድሚያ የሠራተኞቻቸውን ስም ዝርዝርና የምዝገባ ጊዜ ቅድመ ክፍያ ለሀገር ውስጥ ነዋሪዎች 20% በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ዝግ ሂሳብ ገቢ በማድረግ፣ 30%ን መሬቱ በእጃቸው ሲገባ ገቢ የሚያደርጉ መሆናቸውን በመሥሪያ ቤቱ አመራር የተረጋገጠ ሰነድ ማቅረብ አለባቸው፡፡

3. ለእያንዳንዱ ሠራተኛ ወይም ለማህበሩ አባል ለቤቱ የሚከፈለውን ገንዘብ ዝርዝር ሰነድ ፣ አባሉ እንዲሰራለት የፈለገው የቤት ዓይነት፣ የመሬቱ ስፋት፣ የክፍሎች ብዛትና ጠቅላላ ዋጋ የያዘ እንዲሁም የሚያሰራው አካል 50% ክፍያ የከፈለበትን የገንዘብ ደረሰኝና ግንባታውን ለማጠናቀቅ የሚቀረውን 50% ክፍያ ግንባታው እስከሚጠናቀቅ በሂደት ገቢ የሚያደርግ መሆኑን አሠሪው መሥሪያ ቤት ያረጋገጠበት ማስረጃ የሕብረት ሥራ ማህበሩን ለሚያደራጀው አካል ማቅረብ አለበት፡፡

ሐ. ለመኖሪያ ቤት ግንባታ ማህበር የሚያስፈልገውን ክፍያ ለመክፈል አቅም ያላቸውና በማህበር ለመደራጀት ፍላጎት ያላቸውን አርሶ አደሮችና አርብቶ አደሮችን ከዞንና ወረዳ ግብርና ሴክተር ጋር በመሆን በመለየት ሊደራጁበት ለሚፈልጉበት ከተማ ተጽፎ የተረጋገጠ የድጋፍ ደብዳቤ ካቀረቡ በመደራጀት መመዝገብ ይችላሉ፡፡

መ. በቤት ግንባታ ሕብረት ሥራ ማህበር የዲያስፖራውን አደረጃጀት በተመለከተ የፌዴራል ሕብረት ሥራ ማህበር አዋጅ ቁጥር 147/1991 አንቀጽ 9 /2/ ሥር የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ የዚህን መመሪያ ዓላማ ለማስፈጸም ሲባል፣

1. በውጭ ሀገር የሚኖር የሕብረት ሥራ ማህበሩ አባል በአካል መቅረብ የማይችል ከሆነ የታደሰ ፓስፖርት ወይም በትውልድ የኢትዮጵያ ዜጋ መሆኑን የሚገልጽ ማስረጃ ፎቶ ኮፒ ማስረጃ ለመመዝገብና ለማረጋገጥ ሥልጣን ባለው ጽ/ቤትና በውጭ ጉዳይ ሚ/ር ተረጋግጦ በተወካዩ በኩል መቅረብ አለበት፡፡

2. ማንኛውም በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት መስተዳድር ውስጥ በነባሩ ወይም በአዲሱ የመኖሪያ ቤት ግንባታ ሕብረት ሥራ ማህበር መመዝገብ የሚፈልግ ዲያስፖራ ከዚህ መመሪያ ጋር የተያያዘ የመኖሪያ ቤት ፍላጎት የሚገልጽ ማመልከቻ ቅጽ 005 በራሱ ወይም በተወካዩ በኩል ሞልቶ መፈረም አለበት፡፡

3. በአንድ የመኖሪያ ቤት ግንባታ ሕብረት ሥራ ማህበር ውስጥ አንድ ሰው ተወካይ መሆን የሚችለው ለአንድ አባል ብቻ ይሆናል፡፡

4. ለቤት ግንባታ የሚያስፈልገውን ወጪ በተመለከተ ክፍያ የሚፈጸመው በውጭ ሀገር ምንዛሪ ሆኖ ዲያስፖራዉ በቅድሚያ በመኖሪያ ቤት ግንባታ ሕብረት ሥራ ማህበር ስም በተከፈተው የንግድ ባንክ ዝግ ሂሳብ አካውንት 50%ቱን ገቢ ያደርጋል፤ ቀሪውን 50% ደግሞ የመኖሪያ ቤት መሥሪያ መሬት በእጁ ሲገባ ገቢ በማድረግ ያጠናቅቃል፡፡ ገንዘቡን በውጭ ሀገር ምንዛሪ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በተከፈተው ዝግ አካውንት ገቢ የማድረጉ ሥራ በኤምባሲ ወይም በቆንስላና በውጭ ጉዳይ ሚ/ር በኩል የሚፈጸም ይሆናል፡፡

5. ተመላሽ ዲያስፖራ ከሆነ የሚከፈለዉ ገንዘብ በኢትዮጵያ ብር ይሆናል፡፡

3) ምዝገባን በተመለከተ

1. ማንኛዉም የመኖሪያ ቤት ግንባታ ሕብረት ሥራ ማህበር የመመስረቻ ጽሑፍና የመተዳደሪያ ደንቡን አዘጋጅቶ በማቅረብ መመዝገብ ይኖርበታል፡፡

2. አላግባብ ጥቅምና ሕገወጥ ሥራን ለመከላከል እንዲቻል እያንዳንዱ ማህበር በሚወጣው የምዝገባ ኘሮግራም መሠረት የሚያደራጀው አካል ጋ ቀርቦ መመዝገብና አባላቶቹንም ማስመዝገብ አለበት፡፡

3. የመኖሪያ ቤት ግንባታ ሕብረት ሥራ ማህበር እያንዳንዱ አባል በሚወጣው የአሻራ አሰጣጥ ኘሮግራም መሠረት ቀርቦ የጣት አሻራ እንዲሰጥ ያደርጋል፡፡

4. የሕብረት ሥራ ማህበሩ በሚወጣው ኘሮግራም መሠረት ካልተመዘገበና አባላቱን የጣት አሻራ ካለሰጠ እንዳልተደራጀ ይቆጠራል፡፡

## ክፍል አራት

### የቤቶች ዓይነት፣ የግንባታ ዋጋና የሕብረት ሥራ ማህበር አባላት ብዛት

### 9. ለሀገር ውስጥ ነዋሪዎች የቤቶች ዓይነት

1. በከተማ ማዕከል እምብርት ቦታ ላይ ለከተማ መሬት መልሶ የማልማት ኘሮግራም በተያዘው አካባቢ የሚገነቡ ቤቶች የከተማውን ማስተር ኘላንና የክልሉን ልማት መሠረት ያደረገ ሕንፃ ወይም አፓርታማ ይሆናል፡፡

2. ከተማው እየተስፋፋበት ባለው አዲስ አካባቢዎች የሚገነቡ ቤቶች የቦታው ኘላን በሚፈቅደው መሠረት ሆኖ የከተማ ማስተር ኘላንና የአካባቢ ልማት ኘላን ላይ የተመሠረተ ይሆናል፡፡

3. ለአንድ አባል ወይም አባወራ የሚሆን የመሬት ስፋት በአማካይ በካሬ ሜትር፣

ሀ. በአካባቢ በሚገኝ የግንባታ ዕቃ ለሚገነባ ቤት 350 ካሬ ሜትር

ለ. **ቪላ በካሬ ሜትር**

1. በ1ኛና 2ኛ ሀ ደረጃ ከተሞች .... 160 ካሬ ሜትር
2. በ2ኛ ለ ደረጃ ከተሞች .... 180 ካሬ ሜትር
3. በ3ኛሀ ደረጃ ከተሞች .... 200 ካሬ ሜትር

ሐ. ለከተማ ቤት (town house G+1 fi G+2)... 120 ካሬ ሜትር

መ. አፓርታማ ከሆነ ለባለአንድ መኝታ ክፍል 60 ካሬ ሜትር፣ ለባለሁለት መኝታ ክፍል 80 ካሬ ሜትር፣ ለባለሦስት መኝታ ክፍል 100 ካሬ ሜትርና ለባለአራት መኝታ ክፍል 110 ካሬ ሜትር ይሆናል፡፡

ሠ. አንድ የመኖሪያ ቤቶች ግንባታ ሕብረት ሥራ ማህበር ሕንፃ የሚያርፍበት መሬት ስፋት 120 ካሬ ሜትር ይሆናል፡፡

ረ. የመኖሪያ ቤቱ ሥፍራ የጠቅላላ አገልግሎት ቦታ (Common Use) ፓርኪንግ፣ የሕጻናት ስፖርት መጠቀሚያ ቦታና የአረንጓዴ ቦታ ሊኖረዉ ይገባል፡፡

4. በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሕንፃ መመሪያ አንቀጽ 3/3.1.1 ሥር የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ በሌሎች ከተሞችም በልዩ ሁኔታ እንደ ከተማው መሬት ደረጃ ምደባ ተጨባጭ ሁኔታ የማህበሩ ቤት የሚገነባበትና በማህበር የተደራጁ ሰዎችን አቅም ማዕከል ባደረገ አኳኋን የከተማ ከንቲባ ኮሚቴዉ በሚወስነው መሠረት የማህበር ቤቶቹ ከአካባቢው በሚገኘው የግንባታ ዕቃ ሊገነቡ ይችላሉ ፡፡

5. በዩኒየን ሕብረት ሥራ የተደራጁ መሠረታዊ ማህበራት በከተማ መኻከል የአፓርታማ ሕንፃ መገንባት ይችላሉ፡፡

## 10. ለሀገር ውስጥ ነዋሪዎች የቤት ግንባታ ዋጋ ግምት

1. የቤት ግንባታ ሁኔታ አፓርታማ ከሆነ ባለአንድ ክፍል መኝታ ቤት ብር 150 000.00፣ ባለሁለት ክፍል መኝታ ቤት ብር 200 000.00፣ ባለሦስት ክፍል መኝታ ቤት ብር 250 000.00 ና ባለአራት መኝታ ክፍል ቤት ብር 275 000.00 ይሆናል፡፡

2. ለከተማ ቤት (town house) በ80 ካሬ ሜትር ስፋት መሬት ላይ ለሚያርፍ ብር 320 000.00

3. ለቪላ በ80 ካሬ ሜትር ስፋት መሬት ላይ ለሚያርፍ ብር 200 000.00

4. ከአካባቢ ዕቃ ለሚገነባና 80 ካሬ ሜትር መሬት ላይ ለሚያርፍ ቤት ብር 40 000.00 ይሆናል፡፡

5. የቤቶች ግንባታ ዋጋ ግምቱ የማጠናቀቂያ ሥራ ወጪ (Finishing Cost) አይጨምርም፡፡

6. ይህ የግንባታ ዋጋ በወቅቱ ባለው የገበያ ዋጋ ሁኔታ ላይ ተመርኩዞ ሊጨምር ወይም ሊቀንስ ይችላል፡፡

7. የሕዝብ ብዛታቸው ከ10,000 በታች የሆነና የሕንፃ አዋጅ ተፈጻሚነት በማይኖርበት ከተሞች ለጊዜው ሰውን ማኖር የሚችል አንድ ክፍል ቤት ቤቱ ሊገነባበት ከሚችል 80 ካሬ ሜትር መሬት

ውስጥ በ20 ካሬ ሜትር ላይ ያረፈ ቤት ዋጋው ብር 10,000.00 ሆኖ በሂደት ተገንብቶ ማለቅ ያለበትና የማህበሩ አባል የጉልበት ዋጋ በዚህ ወጪ ውስጥ የሚሰላ ይሆናል፡፡

8. ለግንባታ የሚያስፈልግ ወጪ ግምት በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ /1-4/ ሥር የተገለጸ ቢሆንም የሕብረት ሥራ ማህበራቱ በራሳቸው መርጠው ባቀረቡት ዲዛይን ዋጋው በጭማሪው ሊቀየር ይችላል፡፡

## 11. በዲያስፖራ የሚገነቡ የቤቶች ዓይነት

1. በከተማ ማዕከል እምብርት ቦታ ላይ ለከተማ መሬት መልሶ የማልማት ፕሮግራም በተያዘው አካባቢ የሚገነቡ ቤቶች የከተማውን ማስተር ፕላንና የክልሉን ልማት መሠረት ያደረገ ሕንፃ ወይም አፓርታማ ይሆናል፡፡

2. ከተማው እየተስፋፋበት ባለው አዲስ አካባቢዎች የሚገነቡ ቤቶች በቦታው ፕላንና በአካባቢው ልማት ፕላን ላይ የተመሠረተ ይሆናል፡፡

3. ለአንድ አባል ወይም አባወራና እማወራ የሚሆን የመሬት ስፋት በአማካይ በካሬ ሜትር፡-

ሀ. G+1 የከተማ ቤት (town house) 120 ካሬ ሜትር

ለ. Town house G+1 ና G+2 120 ካሬ ሜትርና

ሐ. የከተማ ቤቱ ክፍሎች በማህበሩ አባላት ፍላጎት ላይ የተመሠረቱ ይሆናሉ፡፡

መ. ለባለሁለት መኝታ ክፍል አፓርታማ 80 ካሬ ሜትር፤

ለባለሦስት መኝታ ክፍል 100 ካሬ ሜትርና

ለባለ አራት መኝታ ክፍል 110 ካሬ ሜትር ይሆናል፡፡

4. የአንድ የመኖሪያ ቤት ግንባታ ሕብረት ሥራ ማህበር ሕንፃ የሚያርፍበት መሬት ስፋት 120 ካሬ ሜትር ይሆናል፡፡

5. የመኖሪያ ቤቱ ሥፍራ የጠቅላላ አገልግሎት ቦታ (Common Use) ፓርኪንግ፤ የሕጻናት ስፖርት መጠቀሚያ ቦታና የአረንጓዴ ቦታ ሊኖረዉ ይገባል፡፡

6. በዩኒየን የሚደራጁ የሕብረት ሥራ መሠረታዊ ማህበራት በከተማው መካከል የአፓርታማ ሕንፃ መገንባት ይችላሉ፡፡

## 12. ለዲያስፖራ ቤቶች ግንባታ የዋጋ ግምት

1. የቤቱ ግንባታ ዓይነት አፓርታማ ሆኖ የባለሁለት መኝታ ክፍል ብር 400 000፣ የባለሦስት መኝታ ክፍል ብር 550 000.00 ና የባለአራት መኝታ ክፍል ብር 700 000.00 ይሆናል፡፡

2. ለከተማ ቤት በ80 ካሬ ሜትር ስፋት መሬት ላይ ለሚያርፍ G+1 ና G+2 ብር 800 000.00 ፤

3. የቤቶቹ ግንባታ ዋጋ የማጠናቀቂያ ሥራ ወጪን (Finishing Cost) አይጨምርም፡፡

4. ይህ ከ1-3 የተጠቀሰዉ የግንባታ ወጪ በወቅቱ የገበያ ዋጋ ላይ ተመርኩዞ ሊጨምር ወይም ሊቀንስ ይችላል፡፡

5. ለግንባታ የሚያስፈልግ የወጪ ግምት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1- 4/ ሥር የተገለጸ ቢሆንም የሕብረት ሥራ ማህበራቱ በራሳቸው መርጠው በሚያቀርቡት ዲዛይን ዋጋው ሊቀየር ይችላል፡፡

## 13. የመኖሪያ ቤት ግንባታ ሕብረት ሥራ ማህበር አባላት ብዛት

ሀ. የነባር መኖሪያ ቤት ግንባታ ሕብረት ሥራ ማህበር አባላት ብዛት በተደራጁበት ወቅት ሕጋዊ ሰውነት ባገኙበት የአባላት ብዛት ይሆናል፡፡

ለ. የአዲስ መኖሪያ ቤት ግንባታ ሕብረት ሥራ ማህበር አባላት ብዛት ከ12 አስከ 24 ሊሆን ይችላል፡፡

ሐ. የማህበራቱ አባላት ቁጥር ሙሉ ቁጥር (even number) መሆን አለበት፡፡

## ክፍል አምስት

## የአደረጃጀትና ምዝገባ ሂደት

### 14. የአደረጃጀት ሂደት

1. በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት መስተዳድር ከተሞች ውስጥ ከላይ የተጠቀሱ መስፈርቶችን ያሟላና የሚፈልገውን የቤት ዓይነት የመረጠ አባል የቤት ግንባታ ሕብረት ሥራ ማህበር ለመመዝገብ ሥልጣን ለተሰጠው አካል ዘንድ ቀርቦ በመደራጀት መመዝገብ አለበት፡፡

2. የሕብረት ሥራ ማህበር በነባርና አዲስ የመኖሪያ ቤት ግንባታ ማህበር ተደራጅቶ ለመመዝገብ ሲቀርብ የቤት ፍላጎት ቅጽና የተለያዩ መረጃዎችን መሙላትና ማቅረብን ጨምሮ በሕብረት ሥራ ማህበር አዋጅ ቁጥር 147/1991 አንቀጽ 9 ሥር የተገለጹ መስፈርቶችና የሕብረት ሥራ ማህበሩን በሚያደራጁ አካላት በተጨማሪ የሚጠየቁ መረጃዎችን ሁሉ አጠናቅሮ ቢያንስ በሁለት ኮፒ ማቅረብ አለበት፡፡

3. የቤቶች ግንባታ ሕብረት ሥራ ማህበርን ለመመዝገብ ሥልጣን የተሰጠው አካል ሊመዘገብ የቀረበውን የሕብርት ሥራ ማህበር ለምዝገባ የሚያስፈልጉትን መስፈርቶች ማሟላቱን ካረጋገጠ በኋላ በተመዘገበው የቤቶች ግንባታ ሕብረት ሥራ ማህበር ስም ዝግ የባንክ ሂሳብ (block account) እንዲከፈትለት ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የድጋፍ ደብዳቤ ይጽፋል፡፡

4. የከተማው ነዋሪዎች የቤት ግንባታ ሕብረት ሥራ ማህበር ዝግ የባንክ ሂሳብ (block account) በስማቸው ተከፍቶ ለግንባታ ከሚያስፈልገው ወጪ ውስጥ ለመደራጀት 20% እና መሬት ተዘጋጅቶ የግንባታ ፍቃድ ለመውሰድ 30% በእያንዳንዱ የሕብረት ሥራ ማህበሩ አባል ስም በሕብረት ሥራ ማህበሩ ስም በተከፈተው ዝግ የባንክ ሂሳብ (block account) ገቢ በማድረግና ገቢ ያደረጉበትን ደረሰኝ (SliP) በማቀናጀት እንዲሁም የተቀረውን 50% በግንባታው ሂደት ላይ ተመርኩዞ ግንባታው እስከሚጠናቀቅ የሚከፍሉ መሆኑን ቃል የገቡበት መረጃ የሕብረት ሥራ ማህበሩን ለሚመዘግብ አካል ያቀርባል፡፡

5. የዲያስፖራ የቤት ግንባታ ሕብረት ሥራ ማህበር ዝግ የባንክ ሂሳብ (block account) በስሙ ተከፍቶ ለግንባታ ከሚያስፈልገው ወጪ ውስጥ 50% በእያንደንዱ የሕብረት ሥራ ማህበር አባል

ስም በሕብረት ሥራ ማህበሩ በተከፈተው ዝግ የባንክ ሂሳብ (block account) ገቢ በማድረግ ገቢ ያደረገበትን ደረሰኝ (SliP) በማቀናጀት የሕብረት ሥራ ማህበሩን ለሚመዘግብ አካል ያቀርባል፡፡

6. የቤት ግንባታ ሕብረት ሥራ ማህበር የሚመዘግብ አካል ለምዝገባ የቀረበው የዲያስፖራ ሕብረት ሥራ ማህበር በስሙ በተከፈተው ዝግ የባንክ ሂሳብ (block account) ለግንባታ ከሚፈለገው ወጪ ውስጥ 50% ገቢ ማድረጉን ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በማረጋገጥ ገንዘቡ ባንክ የገባበትን ደረሰኝ ፎቶ ኮፒ ከሕብረት ሥራ ማህበሩና ከእያንዳንዱ አባል ስም ጋር በማያያዝ የግንባታ ቦታ እንዲሰጠው በክልሉ ካቢኔ በተፈቀደው ውሰኔ መሠረት ለከተማ መሬት ልማትና ማኔጅመንት ኤጀንሲ ደብዳቤ ይጽፋል፡፡

7. የከተማ መሬት ልማትና ማኔጅመንት ኤጀንሲ ለቤት ግንባታ የሚውለውን መሬት በክልሉ መንግሥት ካቢኔ ይሁንታ ላይ በመመርኮዝ በቤት ግንባታ ሕብረት ሥራ ማህበሩ ስም መስጠቱን በደብዳቤ ሲያረጋግጥ የሕብረት ሥራ ማህበሩን የሚመዘግብ አካልም መሬት የተሰጠው የሕብረት ሥራ ማህበር የግንባታ ወጪዉን ቀሪ 50% በሕብረት ሥራ ማህበሩ በተከፈተው ዝግ የባንክ አካውንት (block account) በእያንዳንዱ የሕብረት ሥራ ማህበሩ አባል ስም ገቢ በማድረግ 100% እንዲሞሉ በማድረግና በማረጋገጥ የሕብረት ሥራ ማህበሩን መዝግቦ የሕጋዊ ሰውነት መረጃ ሰርቲፊኬት ይሰጣል፣ የግንባታ ፍቃድ እንዲሰጠው ለከተማ ሕንፃ ሹም ደብዳቤ ይጽፋል፡፡

8. በውጭ ሀገር ሆነው በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7 ና 8 ሥር የተገለጹትን መስፈርቶች የሚያሟሉ ዜጎችና ትውልደ ኢትዮጵያውያን የቤት ዓይነት በመምረጥ በቤት ግንባታ የሕብረት ሥራ ማህበር ቀርበው መደራጀት ይችላሉ፡፡ የአደረጃጀታቸው ሁኔታ በኤምባሲ ወይም ባሉበት ሀገር ቆንስላ ወይም በውጭ ጉዳይ በሚመቻቸው ሁኔታ ቀርበው ወይም በሕግ በተወከለው ሰው አማካይነት በመኖሪያ ቤት ግንባታ ሕብረት ሥራ ማህበር ለመደራጀት ይችላሉ፡፡

## 15. ነባር የመኖሪያ ቤት ሕብረት ሥራ ማህበርን ማጠናከር ወይም ማበረታታትን በተመለከተ

1. ከዚህ በፊት ሥልጣን በተሰጠው አካል የመኖሪያ ቤት ግንባታ ሕብረት ሥራ ማህበር ሆኖ ተደራጅቶና ተመዝግቦ የግንባታ መሬት ሳያገኝ የቆየ የመኖሪያ ቤት ግንባታ ሕብረት ሥራ ማህበር በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7 ና 8 ላይ የተገለጸውን ካሟላና የቤት ዓይነት መርጦ ካቀረበ ተመዝግቦ የሕጋዊ ሰውነት ማስረጃ ሰርቲፊኬት ይሰጠዋል፡፡

2. በመኖሪያ ቤት ግንባታ ሕብረት ሥራ ማህበር ተደራጅተው የነበሩ ነባር ማህበራት ያለባቸውን ችግር በማስተካከል አባሎቻቸው ለግንባታ የሚያስፈልጋቸውን ወጪ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7 /6/ ና አንቀጽ 8 /1/ /ለ/ በተገለጸው መሠረት ራሳቸውን ችለው ያለባቸውን የፋይናንስ እጥረት መፍታት ይጠበቅባቸዋል፡፡

3. በዚህ የቤቶች ግንባታ ሕብረት ሥራ ማህበር መመሪያ አንቀጽ 13 ሥር የተጠቀሰው የአባላት ብዛት እንደተጠበቀ ሆኖ ቁጥራቸው አንሶ ከተገኘ የሕብረት ሥራ ማህበር እንዲያደራጅና እንዲመዘግብ ሥልጣን በተሰጠው አካል ተረጋግጦ ከሌሎች ነባር የቤቶች ግንባታ ሕብረት ሥራ ማህበር አባላት ጋር መቀላቀል ይችላሉ፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 3 ሥር የተገለጸው ቢኖር እንኳ የአባላቱ ብዛት ሊቀላቀል የማይችል ከሆነ ወይም የጎደሉት አባላት ቁጥር እናሳ ከሆነ የሕብረት ሥራ ማህበር የሚያደራጅ አካል በፌዴራል ሕብረት ሥራ ማህበር አዋጅ ቁጥር 147/1991 አንቀጽ 6 /3 – 4/ ሥር በተጠቀሰው መሠረት የሕብረት ሥራ ማህበር አባል ከነበሩት ውስጥ ሊተካ ይችላል፡፡

**16. የአዲስ የመኖሪያ ቤት ግንባታ ሕብረት ሥራ ማህበር የምዝገባ አፈጻጸም ሥርዓት**

1. አዳዲስ የመኖሪያ ቤት ግንባታ ሕብረት ሥራ ማህበራት ተደራጅተው ለምዝገባ ሲቀርቡ የተደራጁ አባላት በአንድ አካባቢ የሚኖሩ፣ በአንድ መሥሪያ ቤት ወይም በተቀራራቢ መ/ቤቶች ውስጥ በመሥራት የሚተዋወቁና የጋራ ቤት ለመሥራት በፍቃደኝነት የተደራጁ መሆናቸውን የሚገልጽ ውል የቤቶች ግንባታ ሕብረት ሥራ ማህበር ለማደራጀትና ለመመዝገብ ሥልጣን ለተሰጠው አካል በጽሑፍ ማቅረብ አለባቸው፡፡

2. በመኖሪየ ቤት ግንባታ ሕብረት ሥራ ማህበር መደራጀትና መመዝገብ የሚፈልግ ማንኛውም ሰው ይህን መመሪያ የማክበር ግዴታ አለበት፡፡

3. የነባርና አዲስ የቤቶች ግንባታ ሕብረት ሥራ ማህበር ቤቶች ግንባታ ሥራ የሚፈጸመው፡-

ሀ. ከኦሮሚያ ክልል የቤቶች ግንባታና ልማት ኤጀንሲ ጋር ሕጋዊ ውል በመፈራረም ወይም

ለ. የሕብረት ሥራ ማህበሩ በጨረታ አወዳድሮ በመረጠው ፍቃድ ባለው የግል ሕንፃ ግንባታ ድርጅት ወይም አጥኢ ጋር በተፈራረመው ውል ይሆናል፡፡

ሐ. በዚህ የመኖሪያ ቤት ግንባታ ሕብረት ሥራ ማህበር አፈጻጸም ውስጥ የኦሮሚያ ኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ቢሮ ክትትልና ቁጥጥር ከፍተኛ ድርሻ አለው፡፡

4. ማንኛዉም የመኖሪያ ቤት ግንባታ ሕብረት ሥራ ማህበር እንደማህበር እዉቅና ወይም የሕጋዊ ሰዉነት መረጃ የሚሰጠዉ ተደራጅቶ ቅድመ ክፍያ ፈጽሞ የቤት ግንባታ ቦታ ከተሰጠዉ ብቻ ነዉ፡፡

**ክፍል ስድስት**

**ተግባርና ኃላፊነት**

17. **የመኖሪያ ቤት ግንባታ ሕብረት ሥራ ማህበር አባላት ተግባርና ኃላፊነት**

1. በቤት ግንባታ ሕብረት ሥራ ማህበር ለመደራጀትና ለመመዝገብ የሚፈልግ ማንኛውም ሰው በቅድሚያ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7 ና 8 ሥር የተጠቀሱትን መስፈርቶችና ግዴታዎች በማሟላትና በማክበር በአካል መቅረብ አለበት፡፡ በሕብረት ሥራ ማህበር ተደራጅተው በአካል መቅረብ የማይችሉ የዲያስፖራ አባላት ሕጋዊ ተወካያቸው በአካል መቅረብ አለበት፡፡

2. በዚህ መመሪያ ውስጥ ከተጠቀሰው አግባብ ውጭ መደራጀት፣ መመዝገብ፣ ቤት ማስተላለፍ ...ወዘተ በተመለከተ የማህበሩ አባል በሚፈጽመው ጥፋት ወይም ሕገወጥ ድርጊት በግልም ሆነ በጋራ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

3. ማንኛውም የቤት ግንባታ ሕብረት ሥራ ማህበር አባል በመደራጀትና በምዝገባ ሂደት ውስጥ ከዚህ መመሪያ ውጭ የሚፈጸመውን ማንኛውንም ሕገወጥ ድርጊት የሕብረት ሥራ ማህበር ለሚያደራጀውና ለሚመዘግበው አካል በወቅቱ አቅርቦ የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ ማድረግ አለበት፡፡

4. ማንኛውም የሕብረት ሥራ ማህበር አባል በመረጠው ዲዛይን መሠረት ለግንባታ የሚያስፈልገውን ወጪ በሙሉ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7 /6/ እና አንቀጽ 8 /1/ /ለ/ ሥር በተጠቀሰው መሠረት በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በሕብረት ሥራ ማህበሩ ስም በተከፈተ ዝግ የባንክ ሂሳብ (block account) ገቢ የማድረግ ኃላፊነት አለበት፡፡

5. የሕብረት ሥራ ማህበሩ አባላት በሚጠሩት ስብሰባ ላይ በጊዜ በመገኘት መወያየት፣ ሐሳብ መስጠት፣ መምረጥ፣ መመረጥ፣ አስፈላጊውን ውሳኔ በጋራ ማስተላለፍ፣ የመተዳደሪያ ደንብ

ማውጣትና ማጽደቅ፣ የምስራታ ጽሑፍ ቃለ ጉባኤና ሌሎችን መፈረም፣ የምዝገባና የሼር (መዋጮ) መክፈል፣ የቤት ግንባታና የማህበሩን ሥራ እንቅስቃሴ በግንባታው ሥፍራ በቅርበት መከታተልና መቆጣጠር፣ በጉልበትና በእውቀት ለመደገፍ የግልም ሆነ የጋራ ኃላፊነት አለባቸው፡፡

6. የቤቱ ግንባታ ሲጠናቀቅ በግንባታው ሥፍራ በአካል ወይም በሕጋዊ ተወካይ አማካይነት በመገኘት በዕጣ የወጣላቸውን ቤት መረከብ አለባቸው፡፡

## 18. የመኖሪያ ቤት ግንባታ ሕብረት ሥራ ማህበራት ተግባርና ኃላፊነት

1. የሕብረት ሥራ ማህበሩ አባላት ተመሳሳይ ፍላጎትና አቅም ያላቸው፣ በአንድ አካባቢ በመኖር ወይም በመሥራት የሚተዋወቁ መሆናቸውን በማረጋገጥና አቀራርቦ በማወያየት እንዲዘጋጁ ያደርጋል፡፡

2. የመተዳደሪያ ደንብ፣ የሥራ ዕቅድ፣ የማህበሩ የምሥራታ ጽሑፍ ቃለ ጉባኤና የተለያዩ ተፈላጊ ሰነዶችን አዘጋጅቶ ያቀርባል፡፡

3. የሕብረት ሥራ ማህበሩን አባላት ወክሎ ከማስመዝገብ ጀምሮ ዝግ የባንክ ሂሳብ (block account) እንዲከፈት ማድረግ፣ የመሬትና የግንባታ ዕቃዎች ጥያቄ ያቀርባል፣ ያስፈጽማል፡፡

4. የሕብረት ሥራ ማህበሩን ቤት የሚገነባዉን አካል በመለየት የቤቶች ግንባታና ልማት ኤጀንሲ ከሆነ በውል፣ የግል ተቋራጭ ወይም አጥኢ ከሆነ በጨረታ ይመርጣል፡፡

5. አባላት ለግንባታ የሚያስፈልገውን ወጪ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7 /6/ እና አንቀጽ 8 /1/ /ለ/ መሠረት በሕብረት ሥራ ማህበሩ ስም ቤቱን ለሚገነባው አካል በተፈረመው ውል መሠረት በማጣራት ክፍያ ይፈጽማል፡፡

6. የቤቱ ግንባታ በውሉ መሠረትና በውሉ ደረጃ መፈጸሙን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ ያስተካክላል፡፡

7. የቤት ግንባታው መጠናቀቁ በሕንፃ ሹም ሲረጋገጥ አባላቱ በደረሳቸው ዕጣ መሠረት እንዲወስዱ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣ ቀጣይ የሚሠራውን ሥራ በተመለከተ ሥልጣኑ የተሰጠው አካል የሚያወጣውን መመሪያ ተከታትሎ ይፈጽማል፡፡

8. የሕብረት ሥራ ማህበራት አባላት መብትና ጥቅም ለማስከበር የሕብረት ሥራ ማህበር ከሚያደራጅና ከሚመዘግብ አካል ጋር ይሠራል፡፡

9. የቤቱ ግንባታ ከማህበሩ ጋር በተፈረመው ውል መሠረት የተጠናቀቀ መሆኑ በሕንፃ ሹም ከተረጋገጠ ርክክብ ይፈጽማል፡፡

10. ግንባታው የተጠናቀቀውን ቤት ለማህበሩ አባላት በዕጣ ያስተላልፋል፡፡

## 19. የ1ኛና 2ኛ ደረጃ ከተማ አስተዳደር ተግባርና ኃላፊነት

1. በከተማው የቤቶች ማስተላለፍና ማስተዳደር የሥራ ሂደት ሥር ለመኖሪያ ቤቶች ግንባታ ሕብረት ሥራ ማህበር በሚዋቀረው ቡድን የመኖሪያ ቤቶች ግንባታ ሕብረት ሥራ ማህበር ያደራጃል፤ ይመዘግባል፡፡

2. የመኖሪያ ቤት ግንባታ ሕብረት ሥራ ማህበር አስፈላጊነት፣ የአደረጃጀትና ምዝገባ ሥርዓትና ሂደት በተመለከተ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን በሙሉ ግልጸኝነት ባለው አኳሃን አዘጋጅቶ ማቅረብና መስጠት አለበት፡፡

3. አባላቱ የሚመዘገቡበትን ሂደት፣ የተለያዩ ቅጾችን፣ የምሥራታ ጽሑፍ ቃለ ጉባኤን፣ የመተዳደሪያ ደንብ ሞዴልንና ሌሎች ተፈላጊ ሰነዶችን በማዘጋጀትና ተሞልተው የሚቀርቡበትን ሁኔታ በተመለከተ ለተጠቃሚዎች አስፈላጊውን ማብራሪያና ድጋፍ መስጠት አለበት፡፡

4. ማንኛውም ለምዝገባ የሚያስፈልጉ መስፈርቶችን በሙሉ አሟልቶ የቀረበን የመኖሪያ ቤት ግንባታ ሕብረት ሥራ ማህበር የከተማ መሬት ልማትና ማኔጅመንት ኤጀንሲ የክልሉ መንግሥት ካቢኔ በወሰነው ውሳኔ መሠረት በመኖሪያ ቤቶች ግንባታ ሕብረት ሥራ ማህበር ስም የግንባታ ምደባ መሬት መስጠቱን በማረጋገጥ መዝግቦ የሕጋዊ ሰውነት መረጃ ሰርቲፊኬት ይሰጣል፡፡

5. የተዘጋጀዉ መሬት የሚያስፈልጉ መስፈርቶችን በሙሉ አሟልተዉ የቀረቡትን ማህበራት የማይዳረስ ከሆነ የማህበራቱ ኮሚቴዎች በተገኙበት ዕጣ እንዲጣልላቸዉ ይደረጋል፡፡

6. በሕብረት ሥራ ማህበራት ተሞልተው የቀረቡትን ቅጾችና የተለያዩ ሰነዶች በሕብረት ሥራ ማህበሩ ስም ፋይል በመክፈት በአግባቡ አቀናጅቶ ይይዛል፡፡

7. የመኖሪያ ቤቶች ግንባታ የሕብረት ሥራ ማህበራት አስፈላጊውን ቅድመ ሁኔታና መስፈርት አሟልተው ሲቀርቡ ለሚመለከታቸዉ አካላት የድጋፍ ደብዳቤ ይጽፋል፡፡

8. የመኖሪያ ቤት ግንባታ ሕብረት ሥራ ማህበራት በሕጋዊ መንገድ መመዝገባቸዉን የሚያረጋግጥ የሕጋዊ ሰውነት መረጃ ሰርቲፊኬት (Certificate of Registration) ያዘጋጃል፡፡

9. የማህበሩ አባል በተለያዩ ምክንያቶች ከለቀቀ ወይም ከአባልነት ከተሰረዘ ጉዳዩን በማጣራት ያረጋግጣል፡፡

10. በመሥሪያ ቤቶች አማካይነት የሚገነቡ ቤቶች ሲጠናቀቁ ለተመዘጋቢ አባላት መድረሳቸውን ከመሥሪያ ቤቶቹ ጋር በመሆን ያረጋግጣል፡፡

11. ተደራጅተው የተመዘገቡት የመኖሪያ ቤት ግንባታ ሕብረት ሥራ ማህበራት ሥራ ሲጀምሩ ገቢና ወጪያቸውን በተመለከተ ሂሳባቸዉን በአግባቡ መዝግበው እንዲይዙ ይከታተላል፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ሂሳባቸዉን ሕጋዊ ፍቃድ ባለው ኦዲተር አስመርምሮ ሪፖርቱ እንዲቀርብ ያደርጋል፡፡

12. ተደራጅተው የነበሩ የመኖሪያ ቤት ግንባታ ሕብረት ሥራ ማህበራት በተለያዩ ምክንያቶች ሲፈርሱ በባንክ ዝግ ሂሳብ ተይዞ ያለው ገንዘብ ለአባላቱ እንዲመለስ በማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ተወስኖ ቃለ ጉባኤው ተይዞ ጥያቄ ሲቀርብ ሕጋዊ መሠረት ያለው መሆኑን አረጋግጦ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

13. በአዋጅ፣ ደንብና መመሪያዉ ላይ የተገለጹትን ልዩ ልዩ ተግባሮችና ኃላፊነቶችን ይፈጽማል፡፡

## 20. የዞን ኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ጽ/ቤት ተግባርና ኃላፊነት

1. በጽ/ቤቱ የቤቶች ማስተላለፍና ማስተዳደር ሥራ ሂደት ሥር ለመኖሪያ ቤቶች ግንባታ ሕብረት ሥራ ማህበር በሚዋቀረው ቡድን የ3ኛና 4ኛ ደረጃ ከተሞችን የመኖሪያ ቤት ግንባታ ሕብረት ሥራ ማህበራትን ያደረጃል፣ ይመዘግባል፡፡

2. የ3ኛና 4ኛ ደረጃ ከተማ ነዋሪ ሆነው በመኖሪያ ቤቶች ግንባታ ሕብረት ሥራ ማህበር ለመደራጀት የሚፈልጉ ነዋሪዎችን በመመሪያው ውስጥ በተቀመጠው መስፈርት መሠረት አስፈላጊው መረጃ ተሞልቶ በከንቲባው ፊርማ ተረጋግጦ እንዲቀርብ ያደርጋል፡፡

3. የመኖሪያ ቤት ግንባታ ሕብረት ሥራ ማህበር አስፈላጊነት፣ የአደረጃጀትና ምዝገባ ሥርዓትና ሂደት በተመለከተ አስፈላጊውን መረጃ በሙሉ ግልጸኝነት ባለው አኳሃን አዘጋጅቶ ማቅረብና መስጠት አለበት፡፡

4. አባላቱ የሚመዘገቡበትን ሂደት፣ የተለያዩ ቅጾችን፣ የምሥራታ ጽሑፍ ቃለ ጉባኤን፣ የመተዳደሪያ ደንብ ሞዴልንና ሌሎች ተፈላጊ ሰነዶችን በማዘጋጀትና ተሞልተው የሚቀርቡበትን ሁኔታ በተመለከተ ለተጠቃሚዎች አስፈላጊውን ማብራሪያና ድጋፍ መስጠት አለበት፡፡

5. ማንኛውም ለምዝገባ የሚያስፈልጉ መስፈርቶችን በሙሉ አሟልቶ የቀረበን የመኖሪያ ቤት ግንባታ ሕብረት ሥራ ማህበር የከተማ መሬት ልማትና ማኔጅመንት ኤጀንሲ የክልሉ መንግሥት ካቢኔ በወሰነው ውሳኔ መሠረት በመኖሪያ ቤቶች ግንባታ ሕብረት ሥራ ማህበር ስም የግንባታ ምደባ መሬት መስጠቱን በማረጋገጥ መዝግቦ የሕጋዊ ሰውነት መረጃ ሰርቲፊኬት ይሰጣል፡፡

6. በሕብረት ሥራ ማህበራት ተሞልተው የቀረቡትን ቅጾችና የተለያዩ ሰነዶች በሕብረት ሥራ ማህበሩ ስም ፋይል በመክፈት በአግባቡ አቀናጅቶ ይይዛል፡፡

7. የመኖሪያ ቤቶች ግንባታ የሕብረት ሥራ ማህበራት አስፈላጊውን ቅድመ ሁኔታና መስፈርት አሟልተው ሲቀርቡ ለሚመለከታቸዉ አካላት የድጋፍ ደብዳቤ ይጽፋል፡፡

8. የመኖሪያ ቤት ግንባታ ሕብረት ሥራ ማህበራት በሕጋዊ መንገድ መመዝገባቸዉን የሚያረጋግጥ የሕጋዊ ሰውነት መረጃ ሰርቲፊኬት (Certificate of Registration) ያዘጋጃል፡፡

9. የማህበሩ አባል በተለያዩ ምክንያቶች ከለቀቀ ወይም ከአባልነት ከተሰረዘ ጉዳዩን በማጣራት ያረጋግጣል፡፡

10. በመሥሪያ ቤቶች አማካይነት የሚገነቡ ቤቶች ሲጠናቀቁ ለተመዝጋቢ አባላት መድረሳቸውን ከመሥሪያ ቤቶቹ ጋር በመሆን ያረጋግጣል፡፡

11. ተደራጅተው የተመዘገቡት የመኖሪያ ቤት ግንባታ ሕብረት ሥራ ማህበራት ሥራ ሲጀምሩ ገቢና ወጪያቸውን በተመለከተ ሂሳባቸዉን በአግባቡ መዝግበው እንዲይዙ ይከታተላል፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ሂሳባቸዉን ሕጋዊ ፍቃድ ባለው ኦዲተር አስመርምሮ ሪፖርቱ እንዲቀርብ ያደርጋል፡፡

12. ተደራጅተው የነበሩ የመኖሪያ ቤት ግንባታ ሕብረት ሥራ ማህበራት በተለያዩ ምክንያቶች ሲፈርሱ በባንክ ዝግ ሂሳብ ተይዞ ያለው ገንዘብ ለአባላቱ እንዲመለስ በማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ተወስኖ ቃለ ጉባኤ ተይዞ ጥያቄ ሲቀርብ ሕጋዊ መሠረት ያለው መሆኑን አረጋግጦ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

13. በአዋጅ፣ ደንብና መመሪያዉ ላይ የተገለጹትን ልዩ ልዩ ተግባሮችና ኃላፊነቶችን ይፈጽማል፡፡

## 21. ሠራተኞቻቸው በማህበር የተደራጁ መሥሪያ ቤቶች ተግባርና ሃላፊነት

1. የመኖሪያ ቤት የሌላቸዉ የመሥሪያ ቤቱ ሰራተኞች በመሥሪያ ቤቱ በኩል በማህበር ተደራጅተው ተጠቃሚ እንዲሆኑ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፡፡

2. መሥሪያ ቤቱ ከማህበሩ ኮሚቴ ጋር በመሆን የመሥሪያ ቤታቸውን ሠራተኞች ስም ዝርዝር ማዘጋጀትና ለቤቶች ግንባታ የሚያስፈልገውን ወጪ ሙሉ በሙሉ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ዝግ ሂሳብ በማስገባት ማህበሩን የሚያደራጀዉ አካል ዘንድ በመቅረብ ማህበሩን ያስመዘግባል፣ ቤቱን ለመገንባት የተዋዋለውን አካል ያሳውቃል፡፡

3. የቤቶቹ ግንባታ ሲያልቅ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 17(7) እና አንቀጽ 18(7) መሠረት የሕብረት ሥራ ማህበሩን ካደራጀው አካልና ከማህበሩ ኮሚቴ ጋር በመሆን ግንባታውን ከፈፀመው አካል ላይ ርክክብ ለመፈፀም የወጣውን ወጪ ከግምት ውስጥ በማስገባት በገንዘብ መመለሻ ዉል መሠረት ለማህበሩ አባላት በዕጣ ያከፋፍላል፡፡

4. የመኖሪያ ቤት ግንባታ ሕብረት ሥራ ማህበር አባላት የቤት መሥሪያ ወጪያቸዉ በመሥሪያ ቤታቸው ተከፍሎላቸዉ በተለያዩ ምክንያቶች አባልነታቸዉ ቢቋረጥ በአዋጅ 147/1991 መሠረት የአባሉ መሥሪያ ቤት ወይም ተወካይ ሕብረት ሥራ ማህበሩን ካቋቋመው አካል ጋር በመወያየት በሌላ አባል እንዲተካ ያደርጋል፡፡

22. **በየደረጃዉ ያለዉ የኦሮሚያ ከተማ መሬት ልማትና ማኔጅመንት ኤጀንሲ ተግባርና ኃላፊነት**

1. ለመኖሪያ ቤቶች ግንባታ ሕብረት ሥራ ማህበር በምደባ የሚውል መሬት ባለው ፍላጎት ላይ ተመርኩዞ በወቅቱ በማዘጋጀት ለክልሉ መንግሥት ካቢኔ ለውሳኔ ያቀርባል፡፡

2. በመኖሪያ ቤት ግንባታ ሕብረት ሥራ ማህበር ተደራጅተው ለተመዘገቡ ማህበራት ካደራጃቸው አካል ላይ ጥያቄ ሲቀርብለት ለመኖሪያ ቤት ግንባታ ተዘጋጅቶ በክልሉ ካቢኔ ከተፈቀደዉ መሬት ላይ በ10 ቀናት ውስጥ በሊዝ መመሪያ ቁጥር 9/2005 አንቀድ 31/4 መሠረት መሬት ይሰጣል፣ የመሬት ባለይዞታነት ሰነድ በማህበሩ ስም አዘጋጅቶ በመስጠት ያደራጀዉን አካል ያሳዉቃል፡፡

3. መሬት ለማህበሩ የሚሰጠው በሊዝ መመሪያ ቁጥር 9/2005 አንቀድ 34/1 መሠረት በሊዝ መነሻ ዋጋ ይሆናል፡

4. የተዘጋጀዉ መሬት የሚያስፈልጉ መሰፈርቶችን በሙሉ አሟልተዉ የቀረቡትን ማህበራት የማይዳረስ ከሆነ የማህበራቱ ኮሚቴዎች በተገኙበት ዕጣ እንዲጣልላቸዉ ይደረጋል፡፡

5. ለመኖሪያ ቤት ግንባታ ማህበር የሚሰጠው መሬት መሠረተ ልማቶችን የሟላና ለመኖሪያ ቤት ሥፍራነት ምቹ መሆን አለበት፡፡

6. ፍላጎቱና አቅሙ ላላቸው የሕብረት ሥራ ማህበራትና ዩኒየኖች በከተማ መኻከል ለመልሶ ማልማት ዕቅድ ከተያዘው ላይ ይሰጣቸዋል፡፡

7. የሕብረት ሥራ ማህበሩ የመኖሪያ ቤቶች ግንባታ በተፈቀደው ኘላን መሠረት መጠናቀቁ በአንቀጽ 21 /7/ መሠረት በሕንጻ ሹም ከተረጋገጠ በማህበሩ ስም ይዞታነት ያለውን ካርታ በእያንዳንዱ አባል ስም በማዘጋጀት ይሰጣል፡፡

8. መሬት የተሰጣቸውን የመኖሪያ ቤት ግንባታ ሕብረት ሥራ ማህበራት መረጃ አቀናጅቶ ይይዛል፡፡

**23. የከተማና የዞን ሕንፃ ሹም ተግባርና ኃላፊነት**

1. መሬት የተፈቀደላቸው የቤቶች ግንባታ ማህበራት በግንባታ ደረጃ ፕላን መሠረት እንዲገነቡ የፕላን ውል ማስረጃ ይሰጣል፡፡

2. የፕላን ውል የተሰጣቸው የቤቶች ግንባታ ማህበራት የከተማ ልማት ፕላን መዋቅር እንዲሁም የግንባታው ደረጃ የሚፈልገውን ሕጋዊ ዲዛይን አሟልተዉ ካቀረቡ ተሞልቶ በቀረበው ሕጋዊ ዲዛይን መሠረት መርምሮ በማረጋገጥ በተፈቀደው መሠረት እየተሠራ መሆኑን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ ያስተካክላል፡፡

3. የቤቶች ግንባታ ማህበራት የግንባታ ማሻሻያና እድሳት ጥያቄ ሲያቀርቡ ሕጋዊ መሠረት ያለው መሆኑን በመመርመር ፍቃድ ይሰጣል፡፡

4. የግንባታ ፍቃድ የተሰጣቸውን ማህበራት መረጃ በአግባቡ አቀናጅቶ ይይዛል፡፡

5. የማህበራት ቤቶች ግንባታ የደረሰበትን ደረጃ በማየት በዝግ የባንክ ሂሳብ የተቀመጠላቸው ገንዘብ እንዲለቀቅላቸው በ5 የሥራ ቀናት ውስጥ ማህበሩን ላደራጀው አካል ደብዳቤ ይፅፋል፡፡

6. መሬት የወሰዱና የግንባታ ፍቃድ ያገኙ የሕብረት ሥራ ማህበራት በሕንፃ አዋጅና በገቡት ውል መሠረት ግንባታ መጀመራቸውንና ማጠናቀቃቸውን ይቆጣጠራል፡፡

7. የሕብረት ሥራ ማህበራቱ የቤት ግንባታ በውሉ መሠረት መጠናቀቁን በማረጋገጥ ለማህበሩ አባላት ካርታና ፕላን በየግላቸው ተሠርቶ እንዲሰጣቸው ለከተማ መሬት ልማትና ማኔጅመንት ኤጀንሲ ደብዳቤ ይፅፋል፡፡

8. የቤቱ ግንባታ በተቀመጠለት ስታንዳርድና ዲዛይን ላይ ተመስርቶ መጠናቀቁን ያረጋግጣል፣ ርክክብ እንዲደረግ ለማህበሩ ደብዳቤ ይፅፋል፡፡

## 24. የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ተግባርና ሃላፊነት

1. ለመኖሪያ ቤቶች ግንባታ ሕብረት ሥራ ማህበር ዝግ የባንክ ሂሳብ እንዲከፈት ማህበሩን ያደራጀው አካል በደብዳቤ ሲጠይቅ ዝግ የባንክ ሂሳብ (block account) ይከፍታል፡፡

2. የመኖሪያ ቤት ግንባታ ሕብረት ሥራ ማህበራት የቤት ግንባታ እንዲያከናውን ውል ለፈጸሙለት አካል ገንዘብ እንዲከፈል ማህበራቱን ያደራጀውን አካል በደብዳቤ ሲጠይቁ፣ ያደራጃቸውም አካል ግንባታው ያለበትን ደረጃና ከተጠየቀው ክፍያ ጋር የሚመጣጠን መሆኑን የሕንፃ ሹሙን በደብዳቤ ይጠይቃል፡፡ የሕንፃ ሹሙም ገንዘቡ እንዲከፈል ከፈቀደ ማህበሩን ያደራጀውን አካል በደብዳቤ ይጠይቃል፡፡ ያደራጀዉም አካል ለባንኩ ደብዳቤ በመጻፍ እንዲከፈል ያደርጋል፡፡ ባንኩም በተጻፈለት ደብዳቤ ላይ ተመርኩዞ ክፍያዉን ይፈጽማል፡፡

3. ለዲያስፖራ የቤት ግንባታ ሕብረት ሥራ ማህበራት ከውጭ ጉዳይ ሚ/ርና ከኢትዮጵያ ኤምባሲ ጋር በመሆን ገንዘብ ማስቀመጥ፣ መላክ እንዲሁም ለግንባታ ሥራ ማንቀሳቀስ እንዲቻል የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ቅርንጫፍ በሀገር ውስጥ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፡፡

4. በቤቶች ግንባታ ሕብረት ሥራ ማህበር ተደራጅተው ማህበራቸዉ በተለያዩ ሁኔታዎች የፈረሰባቸዉ በባንክ ዝግ ሂሳብ ያስቀመጡት ገንዘብ እንዲከፈላቸው ሲጠይቁ ወይም አባላት ቢተካኩ ለአደራጁ አካል በሚቀርበው ጥያቄ ተረጋግጦ ያደራጀዉ አካልም ለባንኩ ካቀረበ በባንኩ አሠራር መሠረት በዝግ የባንክ ሂሳብ (block account) ያለው ገንዘብ ለአባላቱ ወይም ለማህበሩ እንዲመለስ ያደርጋል፡፡

5. የመኖሪያ ቤቶች ግንባታ ሀገር ውስጥ ኗሪ ሕብረት ሥራ ማህበር አባላት ለግንባታ የሚሆን 50% ወጪ በእያንዳንዳቸው ስም ገቢ መደረጉን ባንኩ ከረጋገጠ በኋላ በማህበሩ ስም በዝግ የባንክ ሂሳብ (block account) ገቢ አድርጎ ለአደራጁ አካል በደብዳቤ ያሳውቃል፡፡

6. የመኖሪያ ቤቶች ግንባታ ዲያስፖራ ሕብረት ሥራ ማህበር አባላት ለግንባታ የሚሆን 100% ወጪ በእያንዳንዳቸው ስም ገቢ መደረጉን ባንኩ ካረጋገጠ በኋላ በማህበሩ ስም በዝግ የባንክ ሂሳብ (block account) ገቢ አድርጎ ለአደራጁ አካል በደብዳቤ ያሳውቃል፡፡

## 25. የመኖሪያ ቤት ግንባታ ሕብረት ሥራ ማህበራትን ቤት ግንባታ የሚያካሄድ አካል ተግባርና ኃላፊነት

1. በዚህ መመሪያ መሠረት ለቤቶች ግንባታ ከተደራጁ የሕብረት ሥራ ማህበራት ጋር የግንባታ ውል ይፈጽማል፡፡

2. ለግንባታ ማስጀመሪያ የሚያስፈልገውን ገንዘብና ቀሪውን የቤቶቹ ግንባታ ደረጃ በደረሰበት በየደረጃው ከዝግ ሂሳብ ውስጥ እንዲለቀቅለት ይጠይቃል፡፡

3. ከቤቶች ግንባታ ማህበሩ ጋር ቤቶቹን ለመገንባት በተዋዋለበት ውል መሠረት ግንባታውን በዲዛይኑና ስታንዳርዱ መሠረት በጥራትና በተቀመጠለት የጊዜ ገደብ ውስጥ የማጠናቀቅ ግዴታ አለበት፡፡

4. የቤቱ ግንባታ በውሉ መሠረት፣ በስታንዳርዱና በተቀመጠለት ዲዛይን መሠረት መጠናቀቁን የሕንፃ ሹም ካረጋገጠ በኋላ ከማህበሩ ጋር ርክክብ ይፈጽማል፡፡

## 26. የኦሮሚያ ኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ቢሮ ተግባርና ኃላፊነት

1. የመኖሪያ ቤቶች ግንባታ ሕብረት ሥራ ማህበራትን ለመደገፍ ሞዴል፣ መመሪያዎችን፣ የመመሥረቻ ጽሑፍና የመተዳደሪያ ደንብ እንዲሁም የሥራ ማኑዋሎችን የዘጋጃል፡፡

2. ደረጃውን የጠበቀ ዲዛይንና የሚገነባዉን የሕንጻ ታይፖሎጂ እንዲሁም የግንባታ ግምት ያዘጋጃል፤ የቤቶች ግንባታ ሕብረት ሥራ ማህበራት ዲዛይን መርጠው አዘጋጅተው ካቀረቡ ከከተማው ኘላን ጋር የሚጣጣም መሆኑን አይቶ ያረጋግጣል፣ የክትትል አሠራርን ይዘረጋል፡፡ ስልጠናና ግንዛቤ ይሰጣል፤ አፈጻጸሙን ይገመግማል፡፡

3. ለቤቶች ግንባታ ማህበራት በምደባ የሚሰጠው መሬት በወቅቱ ተዘጋጅቶ በክልሉ ካቢኔ እንዲወሰን ድጋፍ ይሰጣል፡፡

4. የቤቶች ግንባታ ሕብረት ሥራ ማህበር ሥራዎች የሚፈጸሙበትን መዋቅርና አደረጃጀት አጥንቶ ይዘረጋል፣ በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፣ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ ያስተካክላል፡፡

5. በማህበር ቤቶች ግንባታ ላይ የሚሠማሩ ተቋራጮች እንዲደራጁ ያደርጋል፣ የአቅም ግንባታና የሙያ ሥልጠና እንዲያገኙ ድጋፍ ያደርጋል፡፡

6. የተለያዩ ባለድርሻ አካላት ቅንጅትና ትስስር በመፍጠር ለመኖሪያ ቤቶች ግንባታ ሕብረት ሥራ ማህበራት የመሠረተ ልማትና ግብዓት አቅርቦት እንዲያሟሉ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፣ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፡፡

7. ተደራጅተው የተመዘገቡ የግንባታ ሥራ ማህበራትን መረጃ አቀናጅቶ ይይዛል፡፡

8. የሕጋዊ ሰውነት ማስረጃንና ማህበራቱ የሚመዘገቡበትን በሕረ መዝገብ በከተሞችና በዞኖች ወጪ ያሳትማል፣ ይሰጣል፡፡

9. በመኖሪያ ቤት ግንባታ ሕብረት ሥራ ማህበር መደራጀት የሚፈልጉ በክልል ደረጃ ያሉ የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሠራተኞችን ያደራጃል፣ ይመዘግባል፤ የሕጋዊ ሰዉነት ማረጋገጫ ይሰጣል፡፡

10. በሠራተኞቹ ፍላጎት መሠረት በሚፈልጉት ከተማ የቤት ግንባታ ቦታ እንዲያገኙ የድጋፍ ደብዳቤ ይጽፋል፣ ይከታተላል፣ ይደግፋል፡፡

11. በውጭ ጉዳይ ሚ/ር በኩል ሙሉ መረጃ ያቀረቡትን ዲያስፖራዎች አጣርቶ ወደ ፈለጉት ከተማ ሄደው እንዲደራጁ የድጋፍ ደብዳቤ ይጽፋል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፣ ይደግፋል፣ ይቆጣጠራል፡፡

12. ማንኛዉንም የመኖሪያ ቤቶች ግንባታ ሕብረት ሥራ ማህበራትን የቤት ግንባታ ሥራ አፈጻጸም ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ ያስተካክላል፡፡

13. በመኖሪያ ቤቶች ግንባታ ሕብረት ሥራ ማህበራት አደረጃጀትና ምዝገባ ላይ ያለዉን አፈጻጸምና ቅሬታ በተመለከተ ከከተማና ዞን መዋቅሮች ጋር በመሆን በቅንጅት በየቀኑ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ ያስተካክላል፡፡

14. ዲያስፖራዉን በመኖሪያ ቤቶች ግንባታ ሕብረት ሥራ ማህበር እንዲያደራጅ ለፌዴራል ዉጭ ጉዳይ ሚንስቴር ዉክልና ይሠጣል፡፡

**ክፍል ሰባት**

**ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች**

**27 ቅድሚያ ተጠቃሚነትን የሚያስገኙ ውሳኔዎች**

1. የቤቶች ግንባታ ሕብረት ሥራ ማህበራት በዚህ መመሪያ መሠረት ተፈላጊ መስፈርቶችን አሟልተው ከተመዘገቡ የቦታ ምደባና ለግንባታ ሂደት የሚደረጉትን ድጋፎች ያገኛሉ፡፡

2. ለመኖሪያ ቤት ግንባታ ሕብረት ሥራ ማህበራት የሚደረገው አገልግሎት የሚወሰነው በተዘጋጀው መሬት ላይ በመመርኮዝ በዕጣ ይሆናል፡፡

3. ሴቶች 30% ቅድሚያ ተጠቃሚዎች ይሆናሉ፡፡

4. የመንግሥት ሠራተኞች 20% ቅድሚያ ተጠቃሚዎች ይሆናሉ፡፡

5. አርሶ አደሮችና አርብቶ አደሮች የቅድሚያ ድጋፍ ያገኛሉ፡፡

**28. ክልከላ**

1. ማህበራትን የማደራጀት ሥልጣን ከተሰጠው አካል በስተቀር ማንኛውም ሰው የመኖሪያ ቤቶች ግንባታ ሕብረት ሥራ ማህበር ማደራጀትና መመዝገብ የተከለከለ ነው፡፡

2. አንድ የቤቶች ግንባታ ሕብረት ሥራ ማህበር አባል በራሱም ሆነ በባለቤቱ ከአንድ ማህበር በላይ ለአባልነት መመዝገብ የተከለከለ ነው ፡፡

3. የመንግሥት ቤቶች ልማት ኘሮግራም ተጠቃሚ በማህበር መደራጀት አይችልም፡፡

4. በአዋጅ 147/1991 አንቀጽ 13 /1/ መሠረት የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ዕዳሜው ከ18 ዓመት በታች የሆነ በራሱም ሆነ በአሳዳጊው ስም ለቤቶች ግንባታ ማህበር መደራጀትም ሆነ መመዝገብ የተከለከለ ነው፡፡

5. በራሱና በባለቤቱ ስም የመኖሪያ ቤት ወይም የመኖሪያ ቤት የሚሠራበት ቦታ ካለውና ከዚህ በፊት በማንኛውም የቤቶች ልማት ኘሮግራም ላይ ተጠቃሚ ከሆነ ወይም ለሦስተኛዉ ወገን

በሽያጭ ካሳለፈ በማንኛውም የቤቶች ግንባታ ማህበር ውስጥ መደራጀትና መመዝገብ የተከለከለ ነው፡፡

## 29. ቅሬታ የሚቀርብበት አካል

የመደራጀትና የምዝገባ ሁኔታን በተመለከተ በሚያደራጀውና በሚመዘግበው አካል ላይ የሚቀርብ ቅሬታ በ10 ቀናት ውስጥ በጽሑፍ ማህበሩን ላደራጀው አካል መቅረብ አለበት፡፡ ያደራጀዉ አካል በሰጠው ውሳኔ ያልረካ አካል ለኦሮሚያ ኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ቢሮ ወይም ለመዋቅሩ (የዞን ኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ጽ/ቤት፤ የከተማ አስተዳደር) የቅሬታ ኮሚቴ ቀርቦ በ15 ቀናት ውስጥ የመጨረሻ ውሳኔ ተሰጥቶ ለቅሬታ አቅራቢው በደብዳቤ ይገለጻል፡፡

## 30. ድጋፍ የመስጠት ግዴታ

ማንኛውም አካል ለዚህ መመሪያ ተፈጻሚነት ድጋፍ የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡

## 31. የወንጀል ቅጣቶች

ማንኛውም ተመዝጋቢ በዚህ መመሪያ ውስጥ የተዘረዘሩትን ጥሶ ከተመዘገበ፣ ሊመዘገብ ከሞከረ፣ ካሳሳተ፣ የምዝገባ ሂደቱን ከረበሸ በወንጀል ሕግ ቅጣት የሚፈጸምበት ወይም በበለጠ የሚያስቀጣው መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፣

1. የተሳሳተ መረጃ መፍጠር፣ መረጃን ወደ ተሳሳተ አቅጣጫ መቀየር ወይም ማጥፋት፣ የመታወቂያ ወረቀት ወይም ሕጋዊ ማሕተም በሕገወጥ መንገድ በመጠቀም /በመሥራት/ ተመዝግቦ ከተገኘ በሀገሪቱ ወንጀለኛ በሚቀጣበት የወንጀል ሕግ ይጠየቃል፡፡

2. በዚህ መመሪያ ከተገለጸው ውጭ በራሱም ሆነ በባለቤቱ ስም ከዚህ በፊት ለመኖሪያ ቤት የሚሆን መሬት ወስዶ የሸጠ ወይም በኮንዶሚኒየም ቤት ዕጣ ተጠቃሚ የሆነና በቤቶች ልማት ኘሮግራም ከአንድ ጊዜ በላይ የተመዘገበ ከሆነ ከሕግ ውጭ ለመበልፀግ በማሰብ ለራሱ ወይም ለሌሎች ሰዎች ጥቅም ለማስገኘት ወይም በሙስና ወይም በማታለል መረጃ የሰጠ ማንኛውም አካል ባለው ሕግ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

3. በወንጀል ሕግ መሠረት ከመንግሥት ሥራ ጋር በተያያዘ ጉዳይ ጉቦ በመስጠት የምዝገባ ሕግ ግዴታዎችን በማሰበርና የመንግሥት ሥራን ለማስተጓጐል ድጋፍ በመስጠት ይህን ግዴታ የጣሰ ማንኛውም ሰው በወንጀል ሕግ ይጠየቃል፡፡

4. ተመዝጋቢው የጣሰው ሕግ ቀላል ከሆነ በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ውስጥ ደንብ በመጣስ በተገለጸው የሕግ ጥሰት ወንጀል መሠረት ተከሶ እንዲቀጣ ይደረጋል፡፡

5. ኃላፊ ወይም የመንግሥት ሠራተኛ በመመሪያው ውስጥ የተደነገጉትን ክልከላ፣ ግዴታና ኃላፊነት ካልተወጣ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሠራተኞች አዋጅና ደንብ መሠረት በዲሲፕሊን ይቀጣል፡፡

6. ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ የወንጀል ሕግ ከሚያስቀጣው አግባብ ውጭ እውነት ያልሆኑ ድርጊቶችን ለመፈጸም ስልጣኑን በሕገውጥ መንገድ ከተጠቀመበት የወንጀል ሕጉን አግባብ በተላለፉ ክስ ይመሰረትበታል፡፡

7. በመንግሥት ሥራ ላይ በደል የፈጸመን የመንግሥት ሠራተኛ ከወንጀል ሕግ አግባብ ውጭ በሕገወጥ መንገድ የመዘገበ እንዲሁም የሚመዘገብ ሠራተኛ፣ የምዝገባ አሠራሩን በመጣስ በመረጃ ላይ በፈጠረው ጥፋት በወንጀል ሕግ አግባብ ክስ ተመስርቶበት እንዲቀጣ ይደረጋል፡፡

## 32. ተፈጻሚነት የሌላቸው መመሪያዎች

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረኑ መመሪያዎችና አሠራሮች በዚህ መመሪያ ውስጥ በታቀፉ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖራቸውም፡፡

## 33. መመሪያውን የማሻሻል ስልጣን

የኦሮሚያ ኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ቢሮ እንደአስፈላጊነቱ ይህን መመሪያ ሊያሻሽል ይችላል፡፡

## 34. መመሪያው ተግባራዊ የሚሆንበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በቢሮው ኃላፊ ተፈርሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ሥራ ላይ የሚውል ይሆናል፡፡

**አብዱልቃድር ሁሴን**

**በም/ፕሬዝዳንት ማእረግ የኦሮሚያ ኢንዱስትርና ከተማ ልማት ቢሮ □ላፊ**

ቀን ---------------------------

ቅጽ 004

**በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት**

የ ---------------------------------------------- ከተማ አስተዳደር/ ዞን ጽ/ቤት

**35. ለመኖሪያ ቤት ግንባታ ሕብረት ሥራ ማህበር አባልነት የተዘጋጀ የማመልከቻ ቅጽ**

1. የሕብረት ሥራ ማህበሩ ስም ------------------------------------------------------------ኃላፊነቱ የተወሰነ የመኖሪያ ቤት ግንባታ ሕብረት ሥራ ማህበር

2. የአመልካች ሁኔታ

2.1 የአመልካች ስም ------------------------------ የአባት ስም ------------------------------

የአያት ስም ---------------------------------- ጾታ ---------- ዕድሜ --------------

ብሔረሰብ ----------------------------

2.2 የእናት ስም --------------- የእናት አባት ስም --------------- የእናት አያት ስም ----------

2.3 የጋብቻ ሁኔታ

ያገባ/ያገባች የፈታ/ የፈታች

ያላገባ/ያላገባች በሞት የተለየ/ የተለየች

2.4 ያገባ/ ያገባች ከሆነ/ች የሚስት/የባል ስም ከነአያት ----------------------------------------

2.5 የአመልካቹ መኖሪያ ሥፍራ

- ክልል ------------------ ከተማ -------------
- ዞን /ክፍለ ከተማ ----------------- ወረዳ -------------------
- ቀበሌ ------------------ የቤት ቁጥር ------------------------

• የቤት ስልክ ቁጥር ---------------- የሞባይል ቁጥር -----------------

• የመታወቂያ ቁጥር /ፓስፖርት/ ቀበሌ/መ/ቤት -------------------------

## 3. የሥራና የገቢ ሁኔታ

3.1 የሥራ ሁኔታ

• የመንግሥት ተቀጣሪ የመንግሥታዊ ያልሆነ/ የግል ድርጅት ተቀጣሪ

• የግል ሥራ

3.2 የሥራ ቦታ

• የመ/ቤት ስም ---------------------------- የሚገኝበት ክልል -------------

• ዞን -------------- ከተማ -------------- ወረዳ -------------------

• የመ/ቤቱ ስልክ ቁጥር ------------------ የፖ.ሣ.ቁ ---------------

3.3 የአመልካች ወራዊ ገቢ /ብር/ --------------------

## 4. የሚፈልጉት ቤት ዓይነትና የክፍሉ ብዛት

4.1 የጋራ ሕንፃ ከሆነ

• ባለ አንድ መኝታ

• ባለ ሁለት መኝታ

• ባለ ሦስት መኝታ

• ባለ አራት መኝታ

• ሌላ

4.2. ባለ አንድ ፎቅ የከተማ ቤት

4.3. ቪላ

4.4. ከአካባቢ ዕቃ የሚገነባ ቤት

8.3 ለምዝገባ ብቁ የሚያደርገኝ ከቤቱ ግንባታ ዋጋ ውስጥ 30% በመደራጀት ጊዜ ፣ ቀሪውን 20% ደግሞ ማህበሩ መሬት ሲያገኝ በዝግ የባንክ ሂሳብ የማስገባ መሆኔን፤

8.4 በከተማው ውስጥ ለተከታታይ ሁለት ዓመታት እየኖርኩ (እየሠራሁ) መሆኔን፣

8.5 የመንግሥት ቋሚ ሠራተኛ መሆኔን፣

8.6 በምወስደው ቤት ውስጥ በጋራ ሕንፃ ሕግ መሠረት ለመኖር ፍቃደኛ መሆኔን፤

8.7 እኔም ሆንኩ ባለቤቴ እየኖርን ያለነው በመንግሥት ቤት ውስጥ ከሆነ ቤቱን ከተረከብኩ በ30 ቀናት ውስጥ ያለሁበትን ቤት ቤቱን ለሚያስተዳድረው አካል ለማስረከብ ፍቃደኛ መሆኔን ፣

8.8 በዚህ የማመልካቻ ቅጽ ላይ የሞላሁት ሐሰት ሆኖ ከተገኘና ቤቱ ከመሠራቱ በፊት ከሆነ ውሉ የሚፈርስ መሆኑንና ቤቱን ከተረከብኩ በኋላ ከሆነ በሕግ ለመጠየቅ የተስማማሁ መሆኔን፣

8.9 ለመደፊት የሚጠየቁ መረጃዎችን ለምሣሌ የጣት አሻራና ሌሎች መረጃዎችን ለመስጠት ፍቃደኛ መሆኔን፣ እንዲሁም

8.10 በተራ ቁጥር 1 ሥር በተጠቀሰው የመኖሪያ ቤት ሕብረት ሥራ ማህበር ስም ከማህበሩ አባላት ጋር በፍላጎቴ ለመደራጀትና የመኖሪያ ቤት ለመሥራት ተፈላጊ ቅድመ ሁኔታና መስፈርት በተቀመጠው አዋጅና መመሪያ መሠረት የሞለሁ በመሆኔ ማህበሩ በአባልነት እንዲቀበለኝና ከዚህ በላይ የሞላሁት መረጃ ሐሰት ሆኖ ከተገኘ በሕግ ተጠያቂ መሆኔን በመስማማት ይህን ቅጽ የሞላሁ መሆኔን በፍርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

የማህበሩ አባል ሙሉ ስም ------------------------------------------

ፊርማ ---------------------------

ቀን --------------------------

**ቀን -----------------------**

**ቅጽ 005**

**በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት**

**የ -------------------------------------------- ከተማ አስተዳደር/ ዞን ጽ/ቤት**

**36. ለመኖሪያ ቤት ግንባታ ሕብረት ሥራ ማህበር አባልነት የተዘጋጀ የዲያስፖራ የማመልከቻ ቅጽ**

1. የሕብረት ሥራ ማህበሩ ስም -----------------------------------------------------------ኃላፊነቱ የተወሰነ የመኖሪያ ቤት ግንባታ ሕብረት ሥራ ማህበር

2. የአመልካች ሁኔታ

   2.1 የአመልካች ስም ------------------------------ የአባት ስም ------------------------------

   የአያት ስም ---------------------------------- ጾታ ---------- ዕድሜ -------------

   ብሔረሰብ ------------------ ዜግነት ---------------- የፓስፖርት ቁጥር ----------------

   2.2 የእናት ስም -------------- የእናት አባት ስም -------------- የእናት አያት ስም ----------

   2.3 የመኖሪያ ሥፍራ

      2.3.1 ሀገር -------------------------

      2.3.2 ከተማ -----------------------

   2.4 የጋብቻ ሁኔታ

   ያገባ/ያገባች የፈታ/ የፈታች

   ያላገባ/ያላገባች በሞት የተለየ/ የተለየች

   2.5 ያገባ/ ያገባች ከሆነ/ች የሚስት/የባል ስም ከነአያት ----------------------------------------

**3. የሚፈልጉት ቤት ዓይነትና የክፍሉ ብዛት**

3.1 የጋራ ሕንፃ ከሆነ

- ባለ አንድ መኝታ
- ባለ ሁለት መኝታ
- ባለ ሦስት መኝታ
- ባለ አራት መኝታ
- ሌላ

3.2 ባለ አንድ ፎቅ የከተማ ቤት

3.3 ቪላ

4. **የተወካይ መረጃ**

4.1 የተወካይ ስም ከነአያት -------------------------------------------------------

4.2 የተወካይ መኖሪያ ሥፍራ

- ክልል ------------------ ከተማ -------------
- ዞን /ክፍለ ከተማ ----------------- ወረዳ -------------------
- ቀበሌ ------------------ የቤት ቁጥር -----------------------
- የቤት ስልክ ቁጥር ---------------- የሞባይል ቁጥር -----------------
- የመታወቂያ ቁጥር /ፓስፖርት/ ቀበሌ/መ/ቤት ------------------------

5. እኔ ስሜ ከላይ የተጠቀሰው አመልካች፤

5.1 ከዚህ በፊት በማንኛውም በመንግሥት በተዘረጋው የቤቶች ልማት ኘሮግራም ውስጥ ያልተመዘገብኩ መሆኔን፣

5.2 በምደራጅበት ከተማ ውስጥ በራሴም ስም ሆነ በሚስቴ ስም (በባሌ ስም) የተመዘገበ የመኖሪያ ቤት ወይም የመኖሪያ ቤት ግንባታ ቦታ የሌለኝና ከዚህ በፊት ያለኝንም በሽያጭ ወይም በስጦታ ለሦስተኛ ወገን ያላስተላለፍኩና ከዚህ በፊት በቤቶች ልማት ኘሮግራም ተጠቃሚ ያልሆንኩ መሆኔን፤

5.3 ለምዝገባ ብቁ የሚያደርገኝ ከቤቱ ግንባታ ዋጋ ውስጥ 50% በመደራጀት ጊዜ ፣ ቀሪውን 50% ደግሞ ማህበሩ መሬት ሲያገኝ በዝግ የባንክ ሂሳብ የማስገባ መሆኔን፤

5.4 በምወስደው ቤት ውስጥ በጋራ ሕንፃ ሕግ መሠረት ለመኖር ፍቃደኛ መሆኔን፤

5.5 እኔም ሆንኩ ባለቤቴ እየኖርን ያለነው በመንግሥት ቤት ውስጥ ከሆነ ቤቱን ከተረከብኩ በ30 ቀናት ውስጥ ያለሁበትን ቤት ቤቱን ለሚያስተዳድረው አካል ለማስረከብ ፍቃደኛ መሆኔን ፣

5.6 በዚህ የማመልካቻ ቅጽ ላይ የሞላሁት ሐሰት ሆኖ ከተገኘና ቤቱ ከመሠራቱ በፊት ከሆነ ውሉ የሚፈርስ መሆኑንና ቤቱን ከተረከብኩ በኋላ ከሆነ በሕግ ለመጠየቅ የተስማማሁ መሆኔን፣

5.7 ለመደፊት የሚጠየቁ መረጃዎችን ለምሣሌ የጣት አሻራና ሌሎች መረጃዎችን ለመስጠት ፍቃደኛ መሆኔን፣ እንዲሁም

5.8 በተራ ቁጥር 1 ሥር በተጠቀሰው የመኖሪያ ቤት ሕብረት ሥራ ማህበር ስም ከማህበሩ አባላት ጋር በፍላጎቴ ለመደራጀትና የመኖሪያ ቤት ለመሥራት ተፈላጊ ቅድመ ሁኔታና መስፈርት በተቀመጠው አዋጅና መመሪያ መሠረት የሞለሁ በመሆኔ ማህበሩ በአባልነት እንዲቀበለኝና ከዚህ በላይ የሞላሁት መረጃ ሐሰት ሆኖ ከተገኘ በሕግ ተጠያቂ መሆኔን በመስማማት ይህን ቅጽ የሞላሁ መሆኔን በፍርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

የማህበሩ አባል ሙሉ ስም ----------------------------------------

ፊርማ -------------------------

ቀን -------------------------